ም ዕ ራ ፍ ፡ ፷፰ ።

አ ፍ ሪ ካ ፡

የጥንት ፡ የአራዊት ፡ ሕዝብ ፡ አገዛዝና ፡ ክርስቲያኖችንም ፡ እንደምን ፡ ይዘርፉዋቸው ፡ እንደ ፡ ነበሩ ።

፩ ፤ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ የተባሉ ፡ ሞሮኮ ፤ አልጀር ፤ ቱኒስና ፤ ትሪፖሊ ፤ ናቸው ። ከሰሜን ፡ ወገን ፡ ከሚዴቴራኒያን ፡ ባሕር ፤ ከምሥራቅና ፡ ከደቡብ ፤ ወገን ፡ ከበረሃው ፡ አገር ፤ ከምዕራብ ፡ ወገን ፡ ከአትላንቲክ ፡ ባሕር ፡ ይዋሰናሉ ። እነዚህ ፡ አገሮች ፡ በሮማውያን ፡ ጊዜ ፡ በሕዝብ ፡ መልተው ፡ ነበሩ ። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሞሮኮ ፡ ሙሪታኒያ ፤ ይባላል ። አልጀርንም ፡ ኑሚዴያ ፡ ይሉታል ። እነዚህን ፡ አገሮች ፡ ፈኒቅያ ፡ ግሪክና ፡ ሌሎችም ፡ አገሮች ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ብለው ፡ ይዘዋቸው ፡ ነበር ።

፪ ፤ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ከተማ ፡ የነበረው ፡ ካርቴጅ ፡ (ቅርጣግና ፡) ያለው ፡ በዚህ ፡ አውራጃ ፡ ነው ። የተሠራበትም ፡ ስፍራ ፡ ከቱኒስ ፡ ከተማ ፡ ዐሥር ፡ ማይል ፡ ርቆ ፡ በሰሜን ፡ ምሥራቅ ፡ ወገን ፡ ነበር ። ከዘመነ ፡ ክርስትና ፡ በፊት ፡ ፮፻፷፬ ፡ ዓመት ፡ ፊንቆናውያን ፡ መሠረቱት ። እንደ ፡ ነገርኋችሁ ፡ ለንግዳቸው ፡ ሲሉ ፡ ንግድንና ፡ ቅኝ ፡ አገርን ፡ በመመሥረት ፡ ቀደምት ፡ የተባሉ ፡ ፊንቆናውያን ፡ ናቸው ።

፫ ፤ ካርቴጅ ፡ (ቅርጣግና ፡) እንዴት ፡ እንደ ፡ ጠፉ ፡ በሮም ፡ ታሪክ ፡ እንግራችኋለሁ ፤ ቀድሞ ፡ በነበረበት ፡ ላይ ፡ ሮማውያን ፡ አዲስ ፡ ከተማ ፡ መሠረቱ ። ይህንንም ፡ ሳራሲኖች ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ አጠፉና ፡ የቱኒስን ፡ ከተማ ፡ ሠሩ ። ባ፲፩፻፫፬ ፡ ቱኒስን ፡ ቱርክ ፡ ያዘው ።

፬ ፤ ባ፲፪፻፵፬ ፡ የአልጀርን ፡ ከተማ ፡ ሳራሲኖች ፡ ሠሩ ፡ የአልጀር ፡ የምስለኔ ፡ አገዛዝ ፡ የተባለውም ፡ ደንብ ፡ ባ፲፭፻፲፰ ፡ ሆሩክና ፡ ኬርዲን ፤ ሐረያዳን ፤ በተባሉ ፡ በሁለት ፡ ቱርክች ፡ ተመሠረተ ። እነዚም ፡ ወንድማማቾች ፡ ነበሩ ። ስማቸውን ፡ ባርባሮሳ ፡ ወይም ፡ ሬድቢርድ ፡ (ቀይ ፡ ጽሕም ፡) ይባላሉ ።

፭ ፤ በኋላ ፡ ሞሮኮ ፡ የተባለውን ፡ አገር ፡ ሳራሲኖች ፡ ድል ፡ አድርገውት ፡ ስለነበር ፡ ወዲያው ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ የያዙትን ፡ ሁሉ ፡ ጨምረው ፡ ያዙት ። ትሪፖሊም ፡ የሆነው ፡ እንዲሁ ፡ ነው ። ከሞሮኮ ፡ በቀር ፡ አያሉት ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ በቱርክ ፡ እጅ ፡ ወደቁ ።

፮ ፤ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ የተባሉት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የማንንም ፡ መርከብ ፡ ማወክ ፡ ሥራቸው ፡ ሆነ ። እየተማረኩም ፡ እንደ ፡ ባርያ ፡ ተሸጡ ። ከተሸጡበትም ፡ ስፍራ ፡ ያለ ፡ ትልቅ ፡ ወጪ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ሊመለሱ ፡ አልቻሉም ።

፯ ፤ ለነዚህ ፡ መጀመሪያ ፡ ነጻ ፡ እንዲወጡ ፡ ያሰበላቸው ፡ አሜሪካ ፡ ነው ። ባ፲፰፻፫ ፡ ኮሞዶር ፡ ፒሪብል ፡ የተባለ ፡ ትንሽ ፡ በሆነ ፡ በአሜሪካ ፡ መርከብ ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ሜዴቴራኒያን ፡ ባሕር ፡ መጥቶ ፡ ትሪፖሊን ፡ ለመያዝ ፡ ከጀለ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከጦር ፡ መርከቦች ፡ አንዱ ፡ ፊላድልፊያ ፡ የተባለው ፡ መርከብ ፡ ተሰብሮ ፡ በወደቡ ፡ ነበር ።

፰ ፡ ፈላድልፊያን ፡ ቱርክች ፡ ይዘው ት ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሴፍተናንት ፡ ዴካቱር ፡ የተባለ ፡ ሌሊት ፡ ፭ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ወደ ፡ ትሪፖሊ ፡ ወደብ ፡ ገባና ፡ ወደ ተማረከው ም ፡ መርከብ ፡ አቃጠ ፡ ቀዘፈ ፡ በደረሰም ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ አብረውት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ እየዘለሉ ፡ ወደ ፡ ተማረከው ፡ መርከብ ፡ ገቡና ፡ በዚያ ፡ ያገኙትን ፡ ቱርክ ፡ ሁሉ ፡ ገደሉ ። የቀሩትንም ፡ እያባረሩ ፡ ከመርከብ ፡ አስወጡዋቸው ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ መርከቡ ፡ ፈላድልፊያ ፡ ተቃጥሎ ፡ ነበር ።

፱ ፡ ከዚህ ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ በኋላ ፡ ኮሞዶር ፡ ፒሬብል ፡ ከናፕል ፡ ንጉሥ ፡ ጥቂት ፡ የመርከብ ፡ መድፎች ፡ አገኘ ። ከነዚህ ፡ ጋር ፡ የአሜሪካንን ፡ መርከቦች ፡ ጨምሮ ፡ የትሪፖሊን ፡ ምሽግ ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ጣለበት ፡ የትሪፖሊ ፡ ባሻ ፡ አስረኞቹን ፡ ለመልቀቅ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ።

፲ ፡ በሺ ፡ ፰፻፲፩ ፡ ፈላድልፊያ ፡ የተባለውን ፡ መርከብ ፡ ያቃጥለ ፡ ኮሞዶር ፡ ዴካቱርን ፡ አልጀርን ፡ እንዲወጋ ፡ ከመርከቦት ፡ ጋር ፡ ሰደዱት ። እርሱም ፡ ታላላቆች ፡ መርከቦቻቸውን ፡ ማረከ ። ዳግመኛም ፡ አሜሪከችን ፡ ባሮች ፡ ብለው ፡ እንዳይ ዙዋቸው ፡ አልጀሪዎችንና ፡ ትሪፖሊታኖችን ፡ አስገደዳቸው ።

፲፩ ፡ ባ፲፰፻፲፮ ፡ በሎርድ ፡ ኤክስሙት ፡ ትእዛዝ ፡ የእንግሊዝ ፡ መርከቦች ፡ መጥተው ፡ አልጀርን ፡ በመድፍ ፡ መቱት ። በአልጀሪዎች ፡ ላይ ፡ ከቶ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ቅጣት ፡ ደርሰባቸው ፡ አያው ቅም ፡ ነበር ። ደግሞ ፡ ባ፲፰፻፴ ፡ ፈረንሳይ ፡ ብዙ ፡ መርከቦችና ፡ ጦር ፡ በማርሻሉ ፡ ቡርሞንት ፡ እግር ፡ አድርጎ ፡ ሰደዶና ፡ የአልጀርን ፡ ምሽግ ፡ አፍርሶ ፡ ከተማዪቱንም ፡ ያዛት ። አሁን ፡ አልጀርያ ፡ የፈረንሳይ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ፤ ግን ፡ በጣም ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ የተገኘ ፡ ነው ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ የተባሉት ፡ የትኞች ፡ ናቸው ፡ ? ከማን ፡ ይዋሰናሉ ፡ ?

፪ ፡ የጥንት ፡ ካርታጎች ፡ ወዴት ፡ ነበሩ ፡ ? ካርታጎን ፡ የመሠረተ ፡ ማነው ፡ ?

፫ ፡ አዲሱን ፡ ከተማ ፡ የመሠረተ ፡ ማነው ፡ ? ሳራሲኖች ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ? ቱኒስ ፡ በቱርክ ፡ የተያዘው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፬ ፡ አልጀርን ፡ ማነው ፡ የሠራው ፡ ? የተሠራውስ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? ባ፲፭፻፲፫ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ? አራዊት ፡ ጨካኞች ፡ የተባሉት ፡ እነማናቸው ፡ ?

፭ ፡ ሞሮኮና ፡ ትሪፖሊ ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ? አራዊት ፡ ከተባሉት ፡ ሕዝብ ፡ በቱርክ ፡ እጅ ፡ የወደቁት ፡ የትኞች ፡ ናቸው ፡ ?

፮ ፡ እነዚህ ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ የሚያደርጉት ፡ የአውሬነት ፡ ሥራቸው ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?

፯ ፡ ባ፲፰፻፲፫ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ? ኮሞዶር ፡ ፒሬብል ፡ የተባለ ፡ ሰውዬ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፰ ፡ ፊላድልፊያ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ዴካቱር ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፱ ፡ በትሪፖሊ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ ወደቁበት ፡ ? ባሻ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፲ ፡ ባ፲፰፻፲፭ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ? ትሪፖሊና ፡ አልጀር ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ስም ምነት ፡ አደረጉ ፡ ?

፲፩ ፡ አልጀር ፡ በመድፍ ፡ የተመታው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

ባ፲፰፻፴ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ? አሁን ፡ አልጀር ፡ ምን ፡ ይታሰባል ፡ ?

ምዕራፍ ፡ ፷፱ ፡ አፍሪካ ።

ስለ ፡ አፍሪካ ተረኑና ነገር ።

፩ ፡ በአፍሪካ ፡ በብዙ ፡ ስፍራና ፡ አውራጃዎች ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ታሪክ ፡ አለ ፡ ይባላል ። ባላገሮቹ ፡ የተጻፈ ፡ ታሪክ ፡ የላቸውም ። ባባቶቻቸው ፡ ዘመን ፡ ይኸና ፡ ይኸ ፡ ተደረገ ፡ ብለው ፡ ለመተረክ ፡ አይችሉም ።

፪ ፡ የቀድሞዎቹ ፡ ስለ ፡ አፍሪካ ፡ ልዩ ፡ ወሳብ ፡ ነበራቸው ። የሚያውቁት ፡ በሰሜን ፡ ወገን ፡ ያለውን ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ የቀረውን ፡ ያልታመነ ፡ ተረት ፡ ብቻ ፡ በመናገር ፡ በቅቶዋቸው ፡ ትተውት ፡ ነበር ። በሥራቅ ፡ ወገን ፡ ባለው ፡ አገር ፡ አፍንጫ ፡ የሌላቸው ፡ ሕዝብ ፡ ያሉ ፡ ይመስላቸው ፡ ነበር ። ለሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ አራት ፡ ዐይን ፡ ያላቸው ፡ ይመስላቸው ፡ ነበር ።

፫ ፡ በአፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ በአንድ ፡ ክፍል ፡ ዐይናቸው ፡ ከደረታቸው ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ጭንቅላት ፡ ብቻ ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፡ ይባል ፡ ነበር ። የቀድሞ ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ አገር ፡ ሲጽፍ ፡ የንጉሣቸው ፡ ራስ ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ራስ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ የነዚሁም ፡ ሕዝብ ፡ ቁመታቸው ፡ ከሰው ፡ ቁመት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ይበልጣል ፡ ብሎ ፡ ነበር ።

፬ ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ታሪክ ፡ ስለ ፡ ድንክች ፡ የሚነገረው ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ትናንሽ ፡ ሕዝቦች ፡ ቁመታቸው ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ቢሆን ፡ ነው ፤ መኖሪያቸው ፡ ነጭ ፡ ዐባይ ፡ ከሚመነጭበት ፡ ነው ፡ ይባላል ። ቤቶቻቸው ፡ እንደ ፡ ዎፍ ፡ ጐጆ ፡ የመሰሉ—ናቸው ። የተሠሩትም ፡ ከጭቃና ፡ ከላባ ፡ ከዛጐል ፡ ነው ።

፭ ፡ እነዚሁ ፡ ድንክች ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሆነው ፡ ታሞራ ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ ያደርጋሉ ። እኩሉ ፡ በበግ ፡ ኮርማ ፡ ላይ ፡ እኩሉ ፡ በፍየል ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ሌሎቹም ፡ በእግር ፡ ሆነው ፡ ይዘምታሉ ።

፮ ፡ የድንክቹ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ካሞራዎቹ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ በተገናኘ ፡ ጊዜ ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ የጀግንነት ፡ ሥራ ፡ ይታያል ። አሞራዎቹ ፡ ክንፋቸውን ፡ እያራገቡ ፡ ወደፊት ፡ ይገፋሉ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ካሞራዎች ፡ ወገን ፡ ድንኩን ፡ እየነጠቁ ፡ ማርከው ፡ በአፋቸው ፡ አንጠልጥለውት ፡ ይሄዳሉ ።

፯ ፡ ድንክቹም ፡ ትናንሽ ፡ ሰይፋቸውንና ፡ ጦራቸውን ፡ እያወዛወዙ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጠላታቸውን ፡ ያባርሩታል ። እንደ ፡ አጋጣሚ ፡ ሆኖ ፡ ዕንቁላላቸውንና ፡ ጫጩታቸውን ፡ ያገኙ ፡ እንደ ሆነ ፡ ዕንቁላሉን ፡ ያፈርጡታል ፡ ጫጩቱንም ፡ ያለ ፡ ምሕረት ፡ ይገድሉታል ።

፰ ፡ እስከ ፕቋት ፡ ዘመን ፡ የአፍሪካን ፡ ውስጥ ፡ ከጥንቶቹ ፡ ይልቅ ፡ የዛሬዎች ፡ ሰዎች ፡ አያውቁትም ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ በዶክቶር ፡ ሊቪንግስቶስ ፡ ምርመራ ፡ በገሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ተመርምሮ ፡ ታውቋል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ነገሩ ፡

የጂዎግራፊ ፣ ጕዳይ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ የታሪክ ፣ ወገን ፣ አይደለም ። በመ፞ኻከለኛው ፣ አፍሪካ ፣ ኒጌር ፣ የተባለው ፣ ወንዝ ፣ በሚፈስበት ፣ ሁሉ ፣ ኒግሪቲያ ፣ ወይም ፣ ኒግሮላንድ ፣ ይባላል ።

፱ ፣ የኒግሪቲያ ፣ ዋናው ፣ ከተማ ፣ ቲምቡክቱ ፣ ይባላል ። ከአንድ ፣ እንግሊዝ ፣ ከአንድ ፣ አሜሪካዊ ፣ ከአንድ ፣ ፈረንሳዊ ፣ ከነዚህ ፣ ከሦስቱ ፣ ነጮች ፣ በቀር ፣ ይህቺን ፣ ከተማ ፣ ሌላ ፣ ነጭ ፣ ሰው ፣ ከቶ ፣ አልረገጣትም ። የኋለኛው ፣ ሰው ፣ ስም ፣ ሙሴ ፣ ሚልዬ ፣ ይባላል ። እሱም ፣ ባ፲፰፻፷፯ ፣ በዚያ ፣ ነበር ። የከተማው ፣ አሠራር ፣ ሦስት ፣ ማዕዘን ፣ ነው ። የተሠራበትም ፣ ስፍራ ፣ ከኒገር ፣ ወንዝ ፣ ስምንት ፣ ማያል ፣ ራቅ ፣ ብሎ ፣ ነው ። ፲፰፻፸፬ ፣ የኒገር ፣ ሁኔታ ፣ ሁሉ ፣ የተገኘው ፣ በላንደር ፣ ወንድሞች ፣ ነው ።

፲ ፣ የቴምቡክቱ ፣ ከተማ ፣ ቤቶች ፣ ከፍታቸው ፣ አንድ ፣ ደርብ ፣ ብቻ ፣ ነው ። ፀሓይ ፣ ባደረቀውና ፣ ክብ ፣ በሆነ ጡብ ፣ ተሠርተዋል ። የተዋረዱት ፣ ሕዝብና ፣ ባሮች ፣ የንብ ፣ ቀፎ ፣ በመሰለ ፣ ሣር ፣ ቤት ፣ ይኖራሉ ። በከተማው ፣ ዙሪያ ፣ ነጭ ፣ ወይም ፣ ብጫ ፣ የመሰለ ፣ አሸዋ ፣ ለበስ ፣ ሰፊ ፣ ሜዳ ፣ አለ ።

፲፩ ፣ በአፍሪካ ፣ ምዕራብ ፣ ጠረፍ ፣ የሚኖሩ ፣ እንግሊዘኞና ፣ ፈረንሳዎች ፣ አሉ ። በዶቡብ ፣ ዳርቻ ፣ ወገን ፣ ቀድሞ ፣ ሆላንዶች ፣ ይኖሩ ፣ ነበር ። ከ፲፰፻፲፮ ፣ ዓመት ፣ ወዲህ ፣ አውራጃውን ፣ እንግሊዝ ፣ ይዘታል ። ይህም ፣ አውራጃ ፣ ኬጵኮሎኒ ፣ ይባላል ። ኬጵኮሎኒም ፣ ያለው ፣ መልካም ፣ ተስፋ ፣ በሚባለው ፣ አውራጃ ፣ በኩል ፣ ነው ።

ጥያቄ ።

፩ ፣ ከአፍሪካ ፣ በሚበዛው ፣ ክፍል ፣ ያሉት ፣ ባላገሮች ፣ ምንድን ፣ ናቸው ፣ ?

፪ ፣ የጥንቱ ፣ ባላገሮች ፣ ስለ ፣ አፍሪካ ፣ ምን ፣ ያስቡ ፣ ይሆን ፣ ?

፬ ፣ ከነዚህ ፣ የሚያሥቁ ፣ ታሪኮች ፣ ሁሉ ፣ የሚያምረው ፣ የትኛው ፣ ነው ፣ ? ስለ ፣ ድንኩች ፣ አንድ ፣ ወሳብ ፣ ተናገር ።

፫ ፣ ስለ ፣ መ፞ኻከል ፣ አፍሪካ የዛሬዎቹ ምን ፣ ያውቃሉ ፣ ? ኒግሪቲያ ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ? ባላገሮቹ ፣ እንዴት ፣ ያሉ ፣ ናቸው ፣ ?

፱ ፣ ቴዎ ቡክቱ ፣ ምንድነው ፣ ? ማነው ፣ ያየው ፣ ? ሙሴ ካሊዬ ፣ ስለዚህ ፣ ምን ፣ ይላል ፣ ? ሁኔታውን ፣ ተናገር ።

፲፩ ፣ ባገሩ ፣ እንደምን ፣ ሰው ፣ ገባበት ? ኬጵኮሎኒ ፣ እንደምን ፣ ሆነ ፣ ? እንግሊዘች ፣ አገሩን ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ዘመን ፣ ይዘውት ፣ ቈዩ ፣ ?

ምዕራፍ ፲ ፣ አፍሪካ ።

ስነ ፣ የባሕር ፣ ጠረፍና ፣ ዶላ ፣ ባርያ ፣ ንግድ ።

፩ ፣ ናታል ፣ የእንግሊዝ ፣ የቅኝ አገር ነው ። ቀድሞ ፣ የኬጵኮሎኒ ፣ ክፍል ፣ ነበር ። በኋላ ፣ ግን ፣ ባ፲፰፻፸፯ ፣ ተኬጵኮሎኒ ፣ ተለየ ። ስፋቱ ፣ ፩፻፱ ፣ ማይል ፣ ይሆናል ። የባሕር ፣ ጠረፍም ፣ አለው ። በዚህ ፣ ስፍራ ፣ ወርቅና ፣ ዕንቊ ፣ በብዙ ፣

ይገኛል ። በአፍሪካ ፣ ምዕራብ ፣ የምትገኝ ፣ ላይቤርያ ፣ የምትባለው ፣ አገር ፣ ነጻ ፣ ሆና ፣ በራስዋ ፣ አዳሪ ፣ ናት ። በሬፑብሊክም ፣ ትገዛለች ። ይህችም ፣ የተመሠረተችው ፣ ባ፲፰፻፵፰ ፣ ዓመት ፣ ነው ። ባ፲፰፻፵፯ ፣ ነጻ ፣ የወጣች ፣ ሬፑብሊክ ፣ ተብላ ፣ ታውጆላታል ። ፯፻ ፣ ማይል ፣ ስፋት ፣ ያለው ፣ የባሕር ፣ ጠረፍም ፣ አግኝታለች ።

፪ ፣ በምዕራብ ፣ አፍሪካ ፣ ጠረፍ ፣ ወገን ፣ ያሉ ፣ የሲኒጋል ፣ አገሮች ፣ ፈረንሳዎች ፣ አሉበት ። ሲኒጋምቢያና ፣ ሲራሊዎን ፣ የባርያ ፣ ንግድን ፣ ለመከልከል ፣ ብለው ፣ እንግሊዞች ፣ ያሉባቸው ፣ አውራጃዎች ፣ ናቸው ። አየሩ ፣ ለአዎሮጵች ፣ የማይስማማ ፣ ጤና ፣ ቢስ ፣ ነው ። የባላገሮቹ ፣ መንግሥት ፣ አሻንቲና ፣ ዳሆሚ ፣ ንጉሣቸው ፣ በዜጎቹ ፣ ላይ ፣ በሚሠራው ፣ የክፋት ፣ ሥራ ፣ የታወቀ ፣ ነው ። እነዚህም ፣ አገሮች ፣ ጊኒያ ፣ አይቮሪኮስት ፣ ጎልድኮካት ፣ ሎጎ ፣ ቤንጉላ ፣ ናቸው ።

፫ ፣ በምሥራቅ ፣ ጠረፍ ፣ ሞዛምቢክ ፣ የፖርቱጊሶች ፣ መኖሪያ ፣ ፋና ፣ አገር ፣ ነው ። በዚህ ፣ አገር ፣ ትልቅ ፣ የጎግድ ፣ ሥራ ፣ ይሠራበታል ። የሞዛምቢክ ፣ ወደብ ፣ ምንም ፣ ችግር ፣ የሌለበት ፣ ነው ። የማዳጋስካር ፣ ደሴት ፣ በምሥራቅ ፣ ጠረፍ ፣ ወገን ፣ ስፋቱ ፣ ፫፻ ፣ ማይል ፣ በማሆን ፣ ባሕር ፣ ተለይቷል ።

፬ ፣ የአፍሪካ ፣ እጅግ ፣ መጥፎው ፣ ታሪክ ፣ የባሪያ ፣ ንግድ ፣ ነው ። በቀድሞው ፣ ዘመን ፣ ሰው ፣ እንደ ፣ ዛሬው ፣ ዘመን ፣ ሳይሠለጥን ፣ በጦርነት ፣ ድል ፣ አድርጎ ፣ የማረከውን ፣ እንደ ፣ ባሪያ ፣ አድርጎ ፣ መያዝ ፣ የተለመደ ፣ ነገር ፣ ነበር ። እንዲህ ፣ ያለውም ፣ ልማድ ፣ እስከ ፣ ብዙ ፣ ዘመናት ፣ ሲደረግ ፣ ቈይቶዋል ። ባርነት ፣ ብዙ ፣ ሽሕ ፣ ዘመን ፣ (ወይም ፣ ብዙ ፣ ዓመታት ፣) በምድር ፣ ላይ ፣ ጸንቶ ፣ ቈይቶዋል ።

፭ ፣ ባ፲፬፻፶፪ ፣ ፖርቱጊሶች ፣ ብርቱ ፣ ንግድ ፣ አድርገው ፣ ባርያ ፣ መሸጥና ፣ መለወጥ ፣ ጀመሩ ። ወዲያው ፣ እንግሊዞች ፣ ደግሞ ፣ ባ፲፮፻፷ ፣ ተከተሉዋቸው ። ነገር ፣ ግን ፣ ባ፲፰፻፴ ፣ የታላቂቱ ፣ ብሪታኒያ ፣ ፓርላሜንት ፣ የባርያ ፣ ንግድ ፣ ፈጽሞ ፣ እንዲቀር ፣ ለባሮች ፣ ጌቶችና ፣ ለሌላም ፣ ጉዳይ ፣ ኻያ ፣ ሚሊዮን ፣ ፓውንድ ፣ ከፈለ ። እንዲህ ፣ ሁኖ ፣ በእንግሊዝ ፣ የቅኝ ፣ አገር ፣ ሁሉ ፣ ለዘለዓለም ፣ ባርነት ፣ ቀረ ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፣ ናታል ፣ በሚባለው ፣ አውራጃ ፣ እንደምን ፣ አድርጎ ፣ ሰው ፣ ገባበት ፣ ? ስለ ፣ ሊቤሪያ ፣ ምን ፣ ትላለህ ፣ ?

፪ ፣ በምዕራብ ፣ አፍሪካ ፣ ጠረፍ ፣ ያሉ ፣ አገሮች ፣ ማን ፣ ያበላሉ ፣ ? ሴራሌዎንም ፣ ለምን ፣ ተያዘ ፣ ?

አየሩ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? አሻንቲና ፣ ዳሆሚ ፣ እንዴት ፣ ሆኑ ፣ ?

፫ ፣ ሞዛምቢክ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? ማዳጋስካር ፣ በምን ፣ ተለየ ፣ ?

፬ ፣ ከአፍሪካ ፣ ታሪክ ፣ ክፉ ፣ ምንድን ፣ ነው ፣ ? የጥንት ፣ ልማዳቸው ፣ ምንድን ፣ ነው ፣ ? ባርነት ፣ እንደምን ፣ ተመሠረተ ፣ ?

፭ ፣ ፖርቱጊሶች ፣ የባርያ ፣ ንግድ ፣ የያመሩት ፣ መቼ ፣ ነው ፣ ? እንግሊዞች ፣ በንግድ ፣ ዙ ከተሉዋቸው ፣ መቼ ነው ፣ ? እንግሊዝ ፣ ምን ፣ (ካሣ)ወጪ ፣ ከፈለ ፣ ?

ምዕራፍ ፣ ፭፩ ፣ መግቢያ ፣ ኤውሮጳ ።

በካርታው ፣ ላይ የታወቁ ፣ ነገሮችና ፣ ሌላም ፣ ነገር ፣ ሁሉ ።

፩ ፣ ኤውሮጳ ፣ የዓለም ፣ ሦስተኛ ፣ ክፍል ፣ ተብሎ ፣ ይታሰባል ፤ በስፋት ፣ ጠባብ ፣ ነው ። የእስያ ፣ አራተኛ ፣ ክፍል ፣ ከአፍሪካም ፣ ከሦስት ፣ አንድ ፣ እጅ ፣ ይሆናል ። ከመላው ፣ ዩናይትድ ፣ እስቴትስ ፣ ከ፫ት ፣ አንድ ፣ እጅ ፣ ይሰፋል ። ይኸውም ፣ የምሥራቅ ፣ የብስ ፣ ክፍል ፣ ነው ። ከእስያ ፣ የሚለየው ፣ ኡራል ፣ የተባለው ፣ ተራራ ፣ ነው ። ከአፍሪካም ፣ የሚለየው ፣ የሚያቴራኒያን ፣ ባሕር ፣ ነው ። በጊብሮልታር ፣ በር ፣ ከኤውሮጳ ፣ እስከ ፣ አፍሪካ ፣ ያለው ፣ ርቀት ፣ ፭፩ ፣ ማይል ፣ ብቻ ፣ ነው ።

፪ ፣ ኤውሮጳ ፣ ካራት ፣ መዓዝነ ፣ ዓለም ፣ በጣም ፣ ያንሳል ። ሁለት ፣ መቶ ፣ ሰማኒያ ፣ ሚሊዮን ፣ ባላገሮች ፣ አሉበት ። በሥልጣኔም ፣ ከእስያና ፣ ከአፍሪካ ፣) በብዙ ፣ ስፍራ ፣ ካሉ ፣ አሜሪከችም ፣ ይበልጣል ። ያማሩ ፣ ከተሞችና ፣ መንገዶች ፤ ጥሩ ፣ ጥሩ ፣ ቤቶችና ፣ ጠቀሜታ ፣ ያላቸው ፣ የእጅ ፣ ሥራዎች ፤ ሌላም ፣ ለሰው ፣ አስፈላጊ ፣ ሆነው ፣ ምቾትና ፣ ደስታ ፣ የሚሰጡ ፣ ነገሮች ፣ ሁሉ ፣ ይገኙበታል ።

፫ ፣ ከቱርክ ፣ በቀር ፣ በኤውሮጳ ፣ በማነኛውም ፣ ክፍል ፣ ሁሉ ፣ የኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ ሃይማኖት ፣ አሸንፎዋል ። በእስያ ፣ ወይም ፣ በአፍሪካ ፣ ውከጥ ፣ ብትሄዱ ፣ ምንም ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ አታገኙም ። ዳሩ ፣ ግን ፣ አልፋችሁ ፣ በአንድ ፣ አንድ ፣ ስፍራ ፣ ለእውነተኛው ፣ አምላክ ፣ የሚሰገድበት ፣ አንድ ፣ አንድ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ታገኛላችሁ ። ለሐሰተኛው ፣ ሃይማኖት ፣ ብለው ፣ ከዕንጨትና ፣ ከደንጊያ ፤ ወይም ፣ ከብረታብረት ፣ ለተሠሩ ፣ ጣዖቶቻቸው ፤ ሕዝቡ ፣ የሚሰግዱበት ፣ ብዙ ፣ ቤተ ፣ ጣዖት ፣ ግን ፣ ታያላችሁ ።

፬ ፣ ነገር ፣ ግን ፣ በኤውሮጳ ፣ የሆነ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ማንም ፣ መንገደኛ ፣ በሚሄድበት ፣ ስፍራ ፣ ሁሉ ፣ አብያተ ፣ ክርስቲያናት ፣ ተሠርተው ፣ ያያል ። የኤውሮጳም ፣ ሕዝብ ፣ ክርስቲያኖች ፣ መሆናቸው ፣ በዚህ ፣ ይታያል ። ደግሞ ፣ በኤውሮጳ ፣ ብዙ ፣ የትምህርት ፣ ቤቶችና ፣ የሊቃውንት ፣ ማኅበሮች ፣ አሉዋቸው ። ይህ ፣ ሁሉ ፣ ሕዝቡ ፣ በሥልጣኔ ፣ ክፍል ፣ ያሉ ፣ መሆናቸውን ፣ ያስረዳል ። ባገኛችሁበት ፣ በዓለም ፣ ክፍል ፣ ሁሉ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያኖች ፣ በ መሠራታቸው ፣ ሕዝቡ ፣ በሥልጣኔና ፣ ሰውን ፣ ደስ ፣ የሚያሰኝ ፣ ጥበብ ፣ በማግኘት ፣ በጣም ፣ ከፍ ፣ ያሉ ፣ መሆናቸውን ፣ ላሳስባችሁ ፣ እወዳለሁ ።

፭ ፣ የክርስቲያን ፣ ሃይማኖት ፣ ሰዎችን ፣ እጅግ ፣ ጠቢባንና ፣ ደስ ፣ ያላቸው ፣ ማድረጉ ፣ በዚህ ፣ ይታወቃል ። የክርስቲያን ፣ ሃይማኖት ፣ ባልታወቀበት ፣ አገር ፣ የሆነ ፣ እንደሆን ፣ ከሕዝቡ ፣ የሚበልጠው ፣ ክፍል ፣ ዕውቀት ፣ የሌለውና ፣ የተዋረደ ፣ ዝቅተኛና ፣ ችጋረኛ ፣ ሕዝብ ፣ ሆኖ ፣ ይቀራል ። ሐሰተኛ ፣ ሃይማኖት ፣ ሰውን ፣ ሁሉ ፣ ይጎዳል ። እውነተኛ ፣ ሃይማኖት ፣ ግን ፣ የሰውን ፣ ወገን ፣ ሁሉ ፣ ወደ ፣ ማሻሻል ፣ ያደርሰዋል ። ስለዚህ ፣ ሰው ፣ ሁሉ ፣ እውነተኛ ፣ ክርስቲያን ፣ ቢሆን ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ዋና ፣ ቁም ፣ ነገር ፣ ይመስላችኋል ። !

፯ ፤ ኤውሮጳ ፣ ከዓለም ፣ ክፍል ፣ ሁሉ ፣ እጅግ ፣ ያነሰች ፣ ናት ። በሰው ም ፣ በሥ ልጣኔም ፣ ከእስያና ፣ ከአፍሪካ ፣ ኋለኛ ፣ ነች ፤ አሰር ፣ ጎይለኛ ፣ ታላቅ ፣ መንግሥት ፣ ከሆነ ፣ በኋላ ፣ ባቢሎንና ፣ ነነዌም ፣ በኤፍራጥስ ፣ ወንዝ ፣ ዳር ፣ ተሠርተው ፣ እጅግ ፣ ከገነኑ ፣ በኋላ ፣ ግብፅም ፣ ታላቅ ፣ ጎይለኛ ፣ መንግሥት ፣ ከሆነች ፣ በኋላ ፣ ቴቤስና ፣ መምፊስ ፣ ሌሎችም ፣ ታላላቆች ፣ ከተሞች ፣ በወባይ ፣ ወንዝ ፣ ዳር ፣ ተሠርተው ፣ በጣም ፣ ከፍ ፣ ካሉ ፣ በኋላ ፣ ዘዋሪዎች ፣ የሆኑ ፣ አራዊት ፣ ሕዝብ ፣ ገና ፣ በኤ ውሮጳ ፣ መግባት ፣ ጀምረው ፣ ነበር ።

፰ ፤ መጀመሪያ ፣ ወደ ፣ ኤውሮጳ ፣ ክፍል ፣ ከገቡት ፣ ፊተኞቹ ፣ ግሪኮች ፣ ነበሩ ። ሙሴ ፣ እስራኤልን ፣ ከግብፅ ፣ ባወጣበት ፣ ዘመን ፣ ቤቶችንና ፣ ከተሞችን ፣ መሥ ራት ፣ ጀመሩ ። ከአውሬነትም ፣ ወጥተው ፣ ወደ ፣ ሥልጣኔ ፣ ደረሱ ። ቀስ ፣ በቀስ ፣ እያለም ፣ ወደ ፣ ዕውቀት ፣ ተራመዱ ። በጣም ፣ የለዘቡ ፣ ሕዝብ ፣ መሆናቸውም ፣ በዓለም ፣ ሁሉ ፣ ታወቀላቸው ።

፱ ፤ ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ሮም ፣ የኢጣሊያ ፣ ታላቅ ፣ ከተማ ፣ ሆነ ። የሮማውያንም ፣ መንግሥት ፣ ከኤውሮጳ ፣ የሚበልጠውን ፣ ክፍልና ፣ በጣም ፣ የሠለጠነውን ፣ የእ ስያንና ፣ የአፍሪካን ፣ ክፍል ፣ ያዘ ። ካርታጎና ፣ ግብፅ ፤ ግሪክ ፤ አሲያሚኖር ፤ ፍልስ ጥኤም ፤ ሶርያ ፤ ከእስያ ፣ ክፍል ፣ የሆኑ ፣ ሌሎችም ፣ አገሮች ፣ ለሮም ፣ ቀንበር ፣ ተንበርክከው ፣ ሰገዱ ።

፲ ፤ ዓለም ፣ ከተመሠረተች ፣ ጀምሮ ፣ እንደ ፣ ሮም ፣ መንግሥት ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ አል ነበረም ። ነገር ፣ ግን ፣ ሌላውን ፣ መንግሥት ፣ ከእግሩ ፣ በታች ፣ እንደ ፣ አደቀቀ ፣ እንዲሁ ፣ ተራውን ፣ የሮምን ፣ የንጉሥ ፣ ነገሥት ፣ መንግሥት ፣ የኤውሮጳ ፣ ሰሜን አውራጃ ፣ መንግሥታት ፣ መዋተው ፣ ከጫማቸው ፣ በታች ፣ ረጋገጡት ። እንዲ ህም ፣ በሆነ ፣ ጊዜ ፣ ወዲያው ፣ ድንቁርና ፣ ተቈራኘው ። ልዩ ፣ ልዩ ፣ ዐይነት ፣ የሆኑ ፣ የኤውሮጳ ፣ ነገድና ፣ ዘሮች ፣ መንግሥት ፣ አካሉና ፣ ቅልጥሙ ፣ ሁለመናው ፣ ተቀጥ ቅጦ ፣ ሕይወት ፣ የሌለው ፣ ይመስል ፣ ነበር ።

፲፤ ነገር ፣ ግን ፣ ተሰባብሮና ፣ ተበታትኖ ፣ ፍርፋሪ ፣ ሆኖ ፣ የነበረው ፣ የሰው ፣ ወገን ፣ ቤተ ፣ ሰብ ፣ በጊዜው ፣ እንደ ፣ ገና ፣ አቈጥቊጦ ፣ አቀጠለና ፣ የተለያየ ፣ ነገድ ፣ ለመ ሆን ፣ በቃ ። አሁን ፣ ያሉበትን ፣ ሁኔታ ፣ እስኪያገኙ ፣ ድረስ ፣ በዕውቀት ፣ ገሥ ግሠው ፣ ለመድረስ ፣ ቻሉ ።

፲፩ ኤውሮጳ ፣ ሰሜንና ፣ ደቡብ ፣ ተብሎ ፣ በሁለት ፣ ተከፍሎዋል ። ቀድሞ ፣ ዘመን ፣ የአየሩ ፣ ቅዝቃዜ ፣ እንደ ፣ መኻከለኛና ፤ እንደ ፣ ምሥራቅ ፣ አሜሪካ ፤ ነበር ። በኋላ ፣ ሙቀቱ ፣ በደቡብ ፣ አገሮች ፣ እንዳለው ፣ ሙቀት ፣ ሆነ ። በሰሜን ፣ ኤው ሮጳ ፣ ያሉት ፣ መንግሥታት ፣ እነዚህ ፣ ናቸው ። ረሺያ ፣ ኖርዌ ፣ ስዊድን ፣ ፕሩሲ ፣ አያሎች ፣ የጀርመን ፣ አገሮች ፣ መንግሥታት ፣ ዳንማርክ ፣ ሆላንድ ቤልጅክ ፣ ስዊትዝርላንድ ፣ ፍራንስ ፣ ታላቂቱ ፣ ብሪታኒያ ።

፲፱ ፣ በደቡብ ፣ ኤውሮጳ ፣ ያሉ ፣ መንግሥታት ፣ እነዚህ ፣ ናቸው ። ፖርቱጋል ፣ እስጴን ፣ ኢጣሊያ ፣ ግሪክ ፣ ቱርክ ፣ የነዚህ ፣ አገሮች ፣ መሬቱ ፣ በጣም ፣ ለም ፣ ነው ። በዚህ ፣ ወይን ፣ ወይራ ፣ በኽረ ፣ ሎሚ ፣ ሎሚ ፣ ሚሎንስ ፣ ሌሎችም ፣ ደስ ፣ የሚያሰኙ ፣ ፍራፍሬዎች ፣ ሁሉ ፣ ተርፈዋል ።

፲፫ ፣ በዚህ ፣ አገር ፣ ለሰው ፣ የሚያስፈልገው ፣ የምግብ ፣ ረገድ ፣ ሁሉ ፣ በቀላል ፣ ይገኛል ። አየሩ ፣ ሙቀት ፣ ሳለ ፣ ደስ ፣ የሚያሰኝ ፣ ነው ። ሕዝቡ ፣ የሚሞቅ ፣ ቤት ፣ ለመሥራት ፣ አያስፈልጋቸውም ፣ ወፍራም ፣ ልብስ ፣ መልበስና ፣ ለክረምትና ፣ ለብርድ ፣ ወራት ፣ የሚያስፈልገውን ፣ ለማሰብ ፣ የታወቀ ፣ ነገር ፣ ነበር ። ይህን ፣ ሁሉ ፣ ሕዝቡ ፣ አስቀድሞ ፣ እንዲያስቡበት ፣ ተፈጥሮ ፣ እንዲህ ፣ አድርጎት ፣ ነበር ። ስለዚህ ፣ የሕዝቡ ፣ ሥራ ፣ በብርድ ፣ አገር ፣ ከሚኖሩት ፣ ይልቅ ፣ ያነሰ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ እንዲሁም ፣ ምቾታቸውና ፣ ደስታቸው ፣ ያነሰ ፣ ሆነ ።

፲፬ ፣ በሰሜን ፣ ኤውሮጳ ፣ ያሉ ፣ ሕዝብ ፣ ግን ፣ ምድርን ፣ በጥንቃቄ ፣ ማረስ ፣ አስፈላጊ ፣ መሆኑን ፣ ስለ ፣ ተረዱት ፣ ረጅም ፣ ለሆነ ፣ ክረምታቸው ፣ አስፈላጊ ፣ የሆነውን ፣ ቀለብ ፣ በጊዜያቱ ፣ ይሰበስባሉ ። መልካሞችን ፣ ቤቶች ፣ ለራሳቸው ፣ ሠርተው ፣ የሚያስፈልጋቸውን ፣ የቤት ፣ መሣሪያ ፣ ያገቡበታል ። እንዲህ ፣ አድርገው ፣ በሥራቸውና ፣ በመጠንቀቃቸው ፣ በደቡብ ፣ በኩል ፣ በመልካም ፣ አየር ፣ ከሚኖሩት ፣ ሕዝብ ፣ ይልቅ ፣ እኒህ ፣ በታላቅ ፣ ደስታ ፣ ይኖራሉ ።

፲፭ ፣ የኤውሮጳ ፣ የዱር ፣ አራዊት ፣ ምንም ፣ ባንዳንድ ፣ ነገር ፣ ቢለያዩ ፣ በአሜሪካ ፣ የሚገኙትን ፣ አራዊት ፣ ይመስላሉ ። ዛፎችና ፣ ቍጥቋጦች ፣ አበቦች ፣ ምንም ፣ ስኳን ፣ ጥቂት ፣ ቢለያዩ ፣ ፍጹም ፣ በአሜሪካ ፣ የሚገኙትን ፣ ይመስላሉ ።

፲፮ ፣ ወደ ፣ አሜሪካ ፣ ብትሄዱ ፣ በየትም ፣ ቢሆን ፣ ወደ ፣ ሌላ ፣ አገር ፣ እንደሆናችሁ ፣ ይሰማችኋል ። ነገር ፣ ግን ፣ ኤውሮጳን ፣ ትዝ ፣ የሚያሰኝና ፣ የሚያሳስባችሁ ፣ ብዙ ፣ ነገር ፣ አለ ። ወደ ፣ እስያ ፣ ወይም ፣ ወደ ፣ አፍሪካ ፣ ብትሄዱ ፣ ቤቶችንና ፣ ሚዳውን ፣ የሕዝቡን ፣ ልብስ ፣ አለባበስ ፣ ልማዳቸውንና ፣ ጠባያቸውን ፣ ስትመለከቱት ፣ ሁለመናው ፣ ከኤውሮጳ ፣ የተለየ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ ሥራሽ ፣ በባዕድ ፣ አገር ፣ መሆናችሁ ፣ ይሰማችኋል ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፣ ሦስተኛው ፣ የዓለም ፣ ክፍል ፣ የተኛው ፣ ነው ፣ ? የሚያንሰው ፣ የዓለም ፣ ክፍል ፣ የተኛው ፣ ነው ፣ ?

ኤውሮጳን ፣ ከእስያ ፣ ጋር ፣ ብናበላልጠው ፣ የቱን ፣ ያህል ፣ ይሰፋል ፣ ?

ከአፍሪካ ፣ ወይም ፣ ከዩናይትድ ፣ እስቴትስ ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ይሰፋል ፣ ?

ከእስያ ፣ በምን ፣ ይለያያል ፣ ? ከአፍሪካስ ፣ ? ለአፍሪካ ፣ የሚቀርበው ፣ የኤውሮጳ ፣ ክፍል ፣ የቱ ፣ ነው ፣ ?

በኤውሮጳና ፣ በአሜሪካ ፣ መኻከል ፣ ያለው ፣ ውቅያኖስ ፣ ማን ፣ ይባላል ፣ ?

ከአሜሪካ ፣ እስከ ፣ ኤውሮጳ ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ይርቃል ፣ ?መልስ ፫ሺ ፣ ማይል ።

፪ ፣ ከኤውሮጳስ ፣ ? የሚዋሰነው ፣ በየት ፣ በኩል ፣ ነው ፣ ?

፫ ፣ የኤውሮጳ ፣ ሃይማኖት ፣ ምንድን ፣ ነው ፣ ? የእስያና ፣ የአፍሪካ ፣ ሃይማኖት ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?
ቤተ ፣ ክርስቲያናቸው ፣ እንዴት ፣ ነው ? መስጊድ ፣ ነውን ፣ ወይስ ፣ ቤተ ፣ መቅደስ ፣ ?

፬ ፣ መንገደኞች ፣ በኤውሮጳ ፣ ሲሄዱ ፣ በየስፍራው ፣ የሚገጥማቸው ፣ (?ሚያገኙት ፣) ምንድነው ፣ ? የቤተ ፣ ክርስቲያኖች ፣ ብዛት ፣ ምን ፣ ያሳያል ፣ ? የትምህርት ፣ ቤቶች ፣ መብዛት ፣ ምን ፣ ያሳያል ፣ ? ቤተ ፣ ክርስቲያኖች ፣ በበዙበት ፣ ስፍራ ፣ ምን ፣ ታገኛለህ ፣ ?

፭ ፣ የክርስቲያን ፣ ሃይማኖት ፣ ምን ፣ ያስገኛል ፣ ? የክርስቲያን ፣ ሃይማኖት ፣ ባልታወቀበት ፣ አገር ፣ ምን ፣ ይሆናል ፣ ? ሐሰተኛ ፣ ሃይማኖት ፣ ምን ፣ ጥቅም ፣ ይሰጣል ፣ ? በውነተኛዪቱ ፣ ሃይማኖት ፣ ምን ፣ ይገኛል ፣ ? ሰው ፣ ሁሉ ፣ እውነተኛ ፣ ክርስቲያን ፣ መሆኑ ፣ ለምንድን ፣ ነው ፣ ?

፮ ፣ ኤውሮጳ ፣ እንደምን ፣ ሆነ ፣ ? የእስያና ፣ የግብፅ ፣ መንግሥታት ፣ ብዙ ፣ ዘመን ፣ እየገነኑ ፣ ሲሄዱ ፣ የኤውሮጳ ፣ ሁኔታ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ?

፯ ፣ በኤውሮጳ ፣ አስቀድሞ ፣ ሰው ፣ የገባበት ፣ የትኛው ፣ ወገን ፣ ነው ፣ ?
ግሪክ ፣ ከአረመኔነት ፣ ወደ ፣ ሥልጥንና ፣ የደረሰው ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ?
ግሪክ ፣ ከፍ ፣ ያለበት ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ?

፰ ፣ ሮም ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? ግዛቱ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? የሮም ፣ መንግሥት ፣ ሲጠፋ ፣ ምን ፣ ተከተለው ፣ ?

፱ ፣ አያሎች ፣ የኤውሮጳ ፣ ሕዝብ ፣ እንዴት ፣ ሆኑ ፣ ?

፲ ፣ ኤውሮጳ ፣ እንደምን ፣ ተከፋፈለ ? የሰሜን ፣ ኤውሮጳ ፣ አየር ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? የደቡብ ፣ ኤውሮጳ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? የሰሜን ፣ ኤውሮጳ ፣ ዋና ፣ ባላገሮች ፣ የተባሉት ፣ እነየቱ ፣ ናቸው ፣ ? ከእንግላንድ ፣ በወዲት ፣ ወገን ፣ ናቸው ፣ ?

፲፩ ፣ የደቡብ ፣ መንግሥታት ፣ እነማናቸው ፣ ? እነዚህ ፣ ከእንግላንድ ፣ በወዲት ፣ ወገን ፣ እንደ ፣ ሆኑ ፣ ታሳያለህን ፣ ?

፲፪ ፣ የደቡብ ፣ ኤውሮጳ ፣ አየር ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

፲፫ ፣ የሰሜን ፣ ኤውሮጳ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? የሕዝቡ ፣ ሁኔታ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

፲፬ ፣ የኤውሮጳ ፣ የዱር ፣ አራዊት ፣ እንዴት ፣ ያሉ ፣ ናቸው ፣ ?
ወደ ፣ አሜሪካና ፣ ወደ ፣ እስያ ፣ ወደ ፣ አፍሪካ ፣ ብትሄድ ፣ ምን ፣ ትሆናለህ ፣ ?

ምዕራፍ ፣ ፫፪ ፣ ኤውሮጳ ።

፩ ፣ ግሪክ ፣ ወደ ፣ ሚዴቴራኒያን ፣ ባሕር ፣ የተዘረጋ ፣ አንድ ፣ ትንሽ ፣ ቊራጭ ፣ አገር ፣ ነው ። ከምሥራቅ ፣ ወደ ፣ ትንሽ ፣ እስያ ፣ ከምዕራብ ፣ ወደ ፣ ኢጣሊያ ፣ አገር ፣ ከሁለቱም ፣ ወገን ፣ ርቀቱ ፣ ትክክል ፣ ነው ።

፪ ፣ ግሪክ ፣ በሰሜን ፣ ወገን ፣ ከመቄዶንያ ፣ ይዋሰናል ። ግሪክ ፣ ዙሪያውን ፣ በባሕር ፣ የታጠረ ፣ ነው ። በደቡብና ፣ በምሥራቅ ፣ ወገን ፣ አያሎች ፣ ደሴቶች ፣ አሉ ። ከነዚህም ፣ ደሴቶች ፣ አንድ ፣ አንዶቹ ፣ እጅግ ፣ ውበት ፣ ናቸው ።

፫ ፣ ከነርሱም ፣ አያሎች ፣ መንደሮችና ፣ ከተሞች ፣ ተሠርተውባቸዋል ። አንዱ ፣ አንቲፖርስ ፣ ይባላል ። በዚህም ፣ ስፍራ ፣ ያለው ፣ ታላቅ ፣ ያጌጠ ፣ ዋሻ ፣ የታወቀ ፣ ስመ ፣ ጥሩ ፣ ነው ። ሺሕ ፣ በሚሆኑ ፣ ባጌጡ ፣ ምሰሶዎች ፣ ተደግፎ ፣ እንደ ፣ ብር ፣ ሲብለጨለጭ ፣ ፋኖስ ፣ አብርታችሁ ፣ ውስጡን ፣ ብታዩት ፣ አንድ ፣ ሰፊ ፣ አዳራሽ ፣ ይመስላል ።

፬ ፣ እኩሌቶቹም ፣ የግሪክ ፣ ደሴቶች ፣ ከባሕር ፣ ወደ ፣ ውጪ ፣ እየተወረወሩ ፣ የወጡ ፣ ይመስላሉ ። እኩሌቶቹም ፣ ከጥንት ፣ ጀምረው ፣ ይታዩ ፣ የነበሩት ፣ ያሉበት ፣ አይታወቅም ፣ ጠፍተዋል ። ይህ ፣ እንግዳ ፣ ነገር ፣ እንዲህ ፣ እንዲሆን ፣ ያደረገው ፣ ከባሕር ፣ በታች ፣ የተነሣው ፣ የቮልካኖ ፣ እሳት ፣ ነው ። አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ከዚህ ፣ ከተፈጥሮ ፣ መናወጽ ፣ የተነሣ ፣ ከሚታዩ ፣ ነገሮች ፣ የበለጠ ፣ የሚያስደንቅ ፣ ነገር ፣ የለም ።

፭ ፣ በደቡብ ፣ ግሪክ ፣ ወገን ፣ ባሉት ፣ ደሴቶች ፣ አየሩ ፣ በአሜሪካ ፣ እንዳለው ፣ እንደ ፣ ቨርጂኒያ ፣ አየር ፣ ቀላል ፣ ነው ። በዚህ ፣ አገር ፣ የሚያስጐመጅ ፣ ብዙ ፣ ፀይነት ፣ ፍሬ ፣ ሁሉ ፣ ሞልቶዋል ። በሰሜን ፣ ወገን ፣ የሆነ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ አየሩ ፣ ቅዝቃዜ ፣ ያለበት ፣ ነው ።

፮ ፣ በግሪክ ፣ አገር ፣ ውስጥ ፣ ለመሄድ ፣ የፈለጋችሁ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ግሪክ ፣ የተፈጥሮ ፣ ውበት ፣ ያለው ፣ አገር ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ታገኙታላችሁ ። በየጠረፉ ፣ ትንንሽ ፣ ባሕሮች ፣ እየሆኑ ፣ የመርከብ ፣ መቋሚያዎች ፣ ወደቦች ፣ ታገኛላችሁ ። በዚያ ፣ የሚኖሩ ፣ ሕዝብ ፣ ባሕሩ ፣ ደስ ፣ ስላሰኛቸው ፣ መርከበኞች ፣ ለመሆን ፣ እንደሚያብላላቸው ፣ ታምናላችሁ ። እንዲሁም ፣ ከባላገሮቹ ፣ ብዙዎቹ ፣ መርከበኞች ፣ ሆነው ፣ ታገኙዋቸዋላችሁ ።

፯ ፣ በደኑም ፣ እንደ ፣ ነገሩ ፣ ፓይን ፣ የተባለው ፣ ጠንካራ ፣ ዛፍ ፣ ይገኛል ። በላይኛው ፣ አውራጃ ፣ አክ ፣ የተባለው ፣ ዛፍ ፣ ይገኛል ። ወደታች ፣ ባለው ፣ ክፍልም ፣ ቸስትነት ፣ ዋልነት ፣ የሚባሉት ፣ ዕንጨቶች ፣ ይገኛሉ ። አታክልት ፣ በተለይ ፣ በጣም ፣ ሞልቶዋል ። ነገር ፣ ግን ፣ የግብርና ፣ ሥራ ፣ ወደ ፣ ኋላ ፣ ቀርቶዋል ።

፰ ፣ በዚህ ፣ ስፍራ ፣ የሚገኘው ፣ ዋናው ፣ ነገር ፣ ደረቅ ፣ ፍራፍሬ ፣ ዘቢብ ፣ ጥጥ ፣ ሐር ፣ ጠጕር ፣ ሩዝ ፣ ትንባሆ ፣ በቆሎ ፣ ነው ። የእጅ ፣ ሥራ ፣ ጥቂት ፣ ነው ።

እጅግም ፡ አያስደንቅ ፤ በቤት ፡ የተለመደ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ጥጥ ፡ እንደ ፡ ጠጕር ፤ እንደ ፡ ሀር ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ነው ። ቀለም ፡ ማግበት ፡ ወይም ፡ መቅበት ፡ በጣም የተለመደ ፡ ከሆነ ፡ ብዙ ፡ ጊዜው ፡ ነው ።

፱ ፤ ከዛፎች ፡ ፍሬ ፡ በጣም ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ብለው ፡ የያዙት ፡ ወይራን ፡ ነው ። ወይራውን ፡ በብዙ ፡ ይተክሉታል ። ወይን ፡ በ[illegible] ፡ ሎሚ ፤ በለስ ፤ አልሞንድ ፤ ተምር ፤ ሴትሮን ፤ ፤ ፖሜግራኔት ፡ ኩሬንት ፤ ግሬፕ ፤ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ አላቸው ።

ጥያቄ ።

፩ ፤ ግሪክ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ነው [illegible] ከጅዮርክ ፡ አኳያ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ? ከታናሽ ፡ እስያ ፡ በየት ፡ አኳያ ፡ ይሆናል ፡ ? ከኢጣሊያ ፡ ከእንግላንድ ፤ ከረሺያ ፤ ከፈረንሳይ ፤ በየት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ?

፪ ፤ ግሪክ ፡ በሰሜን ፡ ወገን ፡ ከማን [illegible] ይዋሰናል ፡ ? ከምሥራቅ ፤ ከደቡብ ፤ ከምዕራብ ፡ ወገን ፡ እንደምን ፡ ይዋሰናል ፡ ?

፫ ፤ ደሴቶቹ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ? አንቲፓሮስ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ?

፬ ፤ ፖልካኖ ፡ የፈነዳባቸው ፡ ደሴቶች ፡ እነማን ፡ ናቸው ፡ ?

፭ ፤ የደቡብ ፡ ግሪክ ፡ አየሩ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? በሰሜን ፡ ወገንስ [illegible] ?

፮ ፤ የግሪክ ፡ ጠረፎች ፡ እንዴት ፡ ናቸው [illegible] ?

፯ ፤ ደኑና ፡ ጫካው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?

፰ ፤ በገሩ ፡ አብልጦ ፡ የሚገኘው ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ? በግሪክ ፡ አገር ፡ የሚገኙትን ፡ ለምግብ ፡ የሚሆኑትን ፡ ፍሬዎች ፡ ተናገር ።

ምዕራፍ ፡ ፸፫ ፡ ኤውሮጳ ።

ስለ ፡ ግሪክ ፡ ስፋትና ፡ መጀመሪያ ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ ሰው ፡ እንዲት ፡ እንደገባበት ።

፩ ፤ በዓለም ፡ ላይ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ከሆኑት ፡ አገሮች ፡ ምንም ፡ ግሪክ ፡ አንዱ [illegible] እርሱ ፡ ቢሆን ፡ አገሩ ፡ ሰፊ ፡ አይደለም ። ወሰኑም ፡ በየጊዜው ፡ ይለዋወጣል [illegible] ርዝመቱ ፡ ካራት ፡ መቶ ፡ ማይል ፤ ስፋቱም ፡ ከመቶ ፡ አምሳ ፡ ማይል [illegible] አይበልጥም [illegible]

፪ ፤ አሁን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንመለስና ፡ ጥንት ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ ሰው [illegible] እንዴት [illegible] እንደ ፡ ገባበትና ፡ ካራት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የሆነውን ፡ እንመልከት [illegible] የሰው ፡ ዘር ፡ ካባቢሎን ፡ ግንብ ፡ በተበተነ ፡ ጊዜ ፡ የኖኅ ፡ የትንሹ ፡ ልጁ ፡ የያፌት ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ ከእስያ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ የተጓዘ ፡ ይመስላል [illegible] ግሪክ ፡ ከሌሎች ፡ የኤውሮጳ ፡ ክፍል ፡ ከሆኑት ፡ አገሮች ፡ ይልቅ ፡ ሰናያር ፡ ለሚባለው ፡ አገር ፡ የቀረበ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በፊት ፡ በዚያ ፡ የገቡ ፡ ይመስላል ።

፫ ፤ የጥንት ፡ አበቶቻቸው ፡ ከምድር ፡ ነው ፡ የወጣነው ፡ ማለታቸውን ፡ ግሪኮች ፡ ራሳቸው ፡ ያምናሉ ። ጥንት ፡ በላገሮቹ ፡ እንደ ፡ አውሬ ፡ የሆኑ ፡ ሕዝብ ፡ ነበሩ ።

መኖሪያቸው ፣ በንድ ፣ ትንሽ ፣ ጐጆ ፣ ውስጥ ፣ ነበር ። ምግባቸውም ፣ የዛፍ ፣ ፍሬ ፣ ነው ፣ ልብሳቸውም ፣ የአውሬ ፣ ቆዳ ፣ ነበር ።

፬ ፤ ስለ ጥንታውያን ግሪክ ፣ ታሪክ ፣ ብዙ ፣ ተረት ፣ ይነገርላቸዋል ። የሦስተኛውንና ፣ ያራተኛውን ፣ መቶ ፣ ዓመት ፣ ባጭሩ ፣ አድርጌ ፣ አልፈዋለሁ ። ሥልጣኔን ፣ መጀመሪያ ፣ ወደ ፣ ግሪክ ፣ አገር ፣ ያገባ ፣ ሴክሮፕስ ፣ የተባለ ፣ አንድ ፣ ግብፃዊ ፣ ነው ፣ ይባላል ። እርሱም ፣ ከአገሩ ፣ ያስከተላቸውን ፣ ይዞ ፣ ወደዚህ ፣ አገር ፣ ገባና ፣ የአቴናን ፣ ከተማ ፣ መሠረተ ። ይህም ፣ የሆነው ፣ ፲፭፻፶፭ ፣ ዓመት ፣ ከዘመን ፣ ክርስትና ፣ በፊት ፣ ነው ።

፭ ፤ ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ፴ ፣ ወይም ፣ ፵ ፣ ዓመት ፣ ቂይቶ ፣ ካድሙስ ፣ ከፊኒቅያ ፣ መጣና ፣ የቴቤስን ፣ ከተማ ፣ ሠራ ። ለግሪክ ፣ ዋና ፣ ጠቃሚ ፣ የሆነ ፣ እርሱ ፣ ነው ። ወይን ፣ የመትከልን ፣ ትምህርት ፤ ብረታብረትን ፣ የመቀጥቀጥ ፣ ብልሀት ፤ የፊደልን ፣ ትምህርት ፣ ጥቅም ፣ ያስተማራቸው ፣ እርሱ ፣ ነው ።

፮ ፤ ሌላውን ፣ የግሪክን ፣ ክፍል ፣ ሌሎች ፣ የውጪ ፣ ነገዶች ፣ የራሳቸው ፣ ቅኝ ፣ አድርገው ፣ ይዘውት ፣ ነበር ። በዚህ ፣ ምክንያት ፣ አገሩ ፣ ስለ ፣ ተከፋፈለ ፣ ርስበርሳቸው ፣ ግንኙነት ፣ የሌላቸው ፣ ትንንሽ ፣ መንግሥታት ፣ ሆኑና ፣ በመካከላቸው ፣ ሁልጊዜ ፣ ጦርነት ፣ ሆነ ።

፯ ፤ ከነዚሁ ፣ ትንንሾች ፣ መንግሥታት ፤ ወይም ፣ አውራጆች ፤ ዐሥራ ፣ ሁለቱ ፣ ቶሎ ፣ ብለው ፣ አንድነት ፣ ተባበሩና መልክተኞቻቸው ፣ በዓመት ፣ ሁለት ፣ ጊዜ ፣ ተሰብስበው ፣ ስለ ፣ አገራቸው ፣ ጉዳይ ፣ እንዲማከሩ ፣ አደረጉ ። ይህም ፣ ጉባኤ ፣ የአምፊዎቲዮንስ ፣ ጉባኤ ፣ ተባለ ። በዚህ ፣ ጉባኤ ፣ ተለያይተው ፣ የነበሩት ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ አውራጃዎች ፣ ርስበርሳቸው ፣ ተስማሙ ። የውጪ ፣ ጠላትም ፣ ቢመጣ ባቸው ፣ ባንድነት ፣ ሁነው ፣ ለመመከት ፣ ጎብረታቸውን ፣ አጸኑ ።

፰ ፤ ከግሪኮች ፣ ታሪክ ፣ ከብዙው ፣ አንዱ ፣ በጣም ፣ የታወቀው ፣ ነገር ፣ ይህ ፣ ነበር ። እርሱም ፣ የአርጎኖቲክ ፣ ዘመቻ ፣ ነው ። ጃሶን ፣ የተባለ ፣ የንጉሥ ፣ ልጅ ፣ ነበር ፣ ይባላል ። እርሱም ፣ ጓደኞቹንና ፣ ወዳጆቹን ፣ አስከትሎ ፣ ከጥቁር ፣ ባሕር ፣ ወደ ፣ ምሥራቅ ፣ ወገን ፣ ኮልቺስ ፣ ወደ ፣ ተባለ ፣ ስፍራ ፣ በመርከብ ፣ ሆኖ ፣ ሄደ ። የሄደበትም ፣ ምክንያት ፣ ጠጕሩ ፣ ወርቅ ፣ የሆነ ፣ አንድ ፣ የሚያስደንቅ ፣ የበግ ፣ ኮርማ ፣ አለ ፣ ብለውት ፣ ያን ፣ ለማግኘት ፣ ነበር ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ይህ ፣ ነገር ፣ ሁሉም ፣ ተረት ፣ ይመስላል ።

፱ ፤ የወርቅ ፣ ጠጕር ፣ ለመፈለግ ፣ ከመዝመት ፣ ይልቅ ፣ የትሮጃ ፣ ጦርነት ፣ እጅግ ፣ ስመ ጥሩ ፣ ነበር ። ትሮጃ ፣ ግለት ፣ ወደ ፣ እስያ ፣ ወገን ፣ ሔሌስፖንት ፣ በሚባል ፣ ስፍራ ፣ አንድ ፣ ትልቅ ፣ ከተማ ፣ ነበር ። ሔሌስፖንት ፣ ዛሬ ፣ ዳርዳኔል ፣ የሚሉት ፣ ጠባብ ፣ ባሕር ፣ ነው ፤ ፓሪስ ፣ የተባለ ፣ የንጉሥ ፣ ትሮጃን ፣ ልጅ ፣ የሚኔሎስን ፤ የግሪክን ፣ ንጉሥ ፣ ልጅ ፣ ሰርቆ ፣ ወስዶ ፣ ነበር ።

፲፤ ይህን ፡ በደል ፡ ለመወጣት ፡ ብለው ፡ የግሪክ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ በአንድነት ፡ ሆኑ ። አንድ ፡ ሺሕ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ መርከቦች ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ትሮጃ ፡ ዘመቱ ። ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ዙሪያውን ፡ ከከበቡት ፡ በኋላ ፡ ከተማውን ፡ ያዙት ፤ ይህም ፡ የሆነ ፡ በ፲፩፻፹፫ ፡ ዓመት ፡ ከዘመነ ፡ ክርስትና ፡ በፊት ፡ ነው ።

፲፩ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሆሜር ፡ እንደሚለው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የትሮጃን ፡ ጦርነት ፡ ትንሽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ የሚያስደንቅ ፡ አይደለም ፡ ይላሉ ።

ጥያቄ ።

፩ ፤ የግሪክ ፡ ስፋት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይሆናል ፡ ? ርዝመቱ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፪ ፤ በግሪክ ፡ ሰው ፡ ተገባ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ይሆናል ፡ ? የግሪክ ፡ የጥንቱ ፡ ሕዝብ ፡ ምን ፡ ኖሯል ፡ ?
ግሪክ ፡ ሰናያር ፡ ከተባለው ፡ አገር ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ? ከግብፅ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?

፫ ፡ ግሪኮች ፡ የጥንት ፡ አባቶቻቸውን ፡ ከወዴት ፡ ወጡ ፡ ይላሉ ፡ ? የጥንት ፡ ግሪክ ፡ ባላገሮች ፡ ምንድን ፡ ናቸው ፡ ?

፬ ፤ ለግሪኮች ፡ ዕውቀትን ፡ ያስተማራቸው ፡ ማነው ፡ ? ሴክሮብስ ፡ የመሠረተው ፡ ከተማ ፡ የትኛውን ፡ ነው ፡ ?
ይኸውስ ፡ የሆነው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? አቴን ፡ ከግሪክ ፡ ከየትኛው ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ? እስከ ፡ ዛሬ ፡ አቴን ፡ አለወይ ፡ ?
መልስ ፡ አምን ፡ አለ ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ከጥንቱ ፡ ጋር ፡ ብናመዛዝነው ፡ የዛሬው ከተማ ፡ በጣም ፡ የተዋረደ ፡ ነው ።
ዙሪያው ፡ በጣም ፡ ያማረ ፡ ነውን ፡ ?

፭ ፤ ካድሙስ ፡ ማነው ፡ ? ቴቤስ ፡ ያለው ፡ ከአቴን ፡ በወዴት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ? በግብፅ ፡ ቴቤስ ፡ የተባለ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ያማረ ፡ ከተማ ፡ መኖሩን ፡ ልብ ፡ አድርጉ ፡ ?

፮ ፤ በሌላው ፡ የግሪክ ፡ ክፍል ፡ ሰው ፡ እንደምን ፡ ገባበት ፡ ? በዚሁ ፡ ዘመን ፡ ግሪክ ፡ እንዴት ፡ ኖሯል ፡ ?

፯ ፤ የግሪክ ፡ ፲፪ ፡ አውራጆች ፡ መንግሥታት ፡ እንዴት ፡ አደረጉ ? የእንፊክቲዎኒክ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፰ ፤ የአርጎናቲክ ፡ ጉዞ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? የትሮጃን ፡ ጦርነት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ሆሜር ፡ እንዴት ፡ ሆነ ።

ምዕራፍ ፡ ፫፬ ፤ ኤውሮጳ ።

ክለ ፤ ግሪኮች ፡ ኑግ ፡ አውጪ ፡ (ሐጋጊ ፡)

፩ ፤ ግሪኮች ፡ ቀና ፡ መንግሥታቸውን ፡ እስፓርታ ፤ ወይም ፡ ለሲዴሞን ፡ ይሉታል። ከክርስቶስ ፡ በፊት ፡ ፲፭፻፲፯ ፡ ዓመት ፡ ሌሌክስ ፡ የተባለ ፡ መሠረተው ። ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ በፊት ፡ ከነበረ ፡ ሊኩርጉስ ፡ ከተባለ ፡ ሰው ፡ የደን

ብንና ፣ የሕግን ፣ ሥርዓት ፣ ተቀበለ ። እርሱም ፣ ደንብን ፣ ጠባቂና ፣ በነገሩ ሁሉ ፡ የጸና ፤ ቀጥታ ፣ ያለው ፣ ሰው ፣ ሆኖ ፣ ሳለ ፣ ደግሞ ፣ ብልህና ፣ ቅንነት ፣ ያለው ፡ ሰው ፣ ነበር ።

፪ ፤ ሊኩርጉስም ፣ የስፓርታ ፣ ሰው ፣ ሁሉ ፣ በአንድነት ፣ ሆኖ ፣ ምግቡን ፣ በግልጽ ፡ በውጪ ፣ ባደባባይ ፣ ይብላ ፣ የሚል ፣ ደንብ ፣ አወጣ ። የዚህም ፣ ደንብ ፣ ምሥጢር ፣ ሀብታሞች ፣ የሆኑት ፣ በቤታቸው ፣ የከበረ ፣ ምግብ ፣ እየበሉ ፣ ብቻቸውን ፡ እንዳይፈነጥዙ ፤ ድኾችና ፣ ሀብታሞች ፣ በንድነት ፣ ሆነው ፣ እየበሉ ፣ ትክክል ፡ እንዲሆኑ ፣ ነው ። ለሕፃናት ፣ የሆነ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ካልሰረቁ ፣ በቀር ፣ አንዳች ፡ የሚበሉት ፣ እንዲያገኙ ፡ አልተፈቀደላቸውም ፣ ነበር ። ይህንም ፣ መጥር ፣ ልማድ ፡ ማቆማቸው ፣ እስፓርቶች ፣ በጦርነት ፣ ጊዜ ፡ ብልጦች ፣ እንዲሆኑ ፣ ነው ።

፫ ፤ በሕዝቡ ፣ ንፍገትና ፣ ስስት ፣ እንዳያድርባቸው ፣ ብርና ፣ ወርቅ ፣ ተቀርጾ ፡ ገንዘብ ፣ ተብሎ ፣ እንዳይወጣ ፣ ሊኩርጉስ ፣ አስከለከለ ። ገንዘብ ፣ የሚባል ፣ ብረት ፡ ብቻ ፣ እንዲሆን ፣ አደረገ ። የእስፓርቶች ፣ ብር ፣ በሚዛን ፣ አምሳ ፣ ፓውንድ ፣ በነሣ ፡ ይከብድ ፣ ነበርና ፣ በኪስ ፣ ለመያዝ ፣ አይመችም ፣ ነበር ።

፬ ፤ ልጆች ፣ ሁሉ ፣ የሚያድጉት ፣ በሕዝብ ፣ ኪሣራ ፣ ነው ። ግብር ፣ ሲበላ ፣ በጎ በታው ፣ ዙሪያ ፣ ቁመው ፣ ጥበብ ፣ የመላበትን ፣ ያባቶቻቸውን ፣ ንግግርና ፡ ጨዋታ ፣ እንዲሰሙ ፡ ተፈቅዶላቸዋል ። እስፓርቶች ፣ ልጆቻቸው ፣ ስካርን ፣ እን ዲጸየፉ ፣ በጣም ፣ ያሠጓቸው ፣ ነበር ።

፭ ፤ ይህን ፣ ስካር ፣ የሚያመጣውን ፣ የሚያስጸይፍ ፣ ነገር ፣ ያሳዩዋቸዋል ። ሲያሳ ዩዋቸውም ፣ እንደዚህ ፣ አድርገው ፣ ነው ፤ በፊት ፣ አንዱን ፣ ባሪያ ፣ አረቄ ፣ ያጠ ጡና ፣ ያሰክሩታል ፤ ልጆቹም ፣ የሰከረው ፣ ባሪያ ፣ የሚሆነውን ፣ ሁኔታ ፣ ሁሉ ፡ በዐይናቸው ፣ ከተመለከቱ ፣ በኋላ ፤ እንደዚህ ፣ ያለ ፣ ውርደት ፣ ወደሚያመጣ ፡ ነገር ፣ እንዳይወድቁ ፣ ራሳቸው ፣ ይጠነቀቃሉ ።

፮ ፤ ሊኩርጉስ ፣ ለአገሩ ፣ ሰዎች ፣ ሕግና ፣ ደንብ ፡ ከሰጣቸው ፣ በኋላ ፣ ከእስፓ ርታ ፣ ተነሥቶ ፣ ሄደ ። ነገር ፣ ግን ፣ ገና ፣ ሊነሣ ፣ ሲል ፣ ሕዝቡን ፣ ሰብስቦ ፣ እስኪ መለስ ፣ ድረስ ፣ የሰጠኋችሁን ፣ ሕግ ፣ እንዳትለውጡ ፣ ብሎ ፣ አስማላቸው ። ነገር ፡ ግን ፣ እንዳይመለስ ፣ ቍርጥ ፣ አሳብ ፣ አድርጎ ፣ ነበር ።

፯ ፤ ሰውነቱን ፣ በረኃብ ፣ ገደለ ፤ ራሳውን ፣ እስፓርቶች ፣ እንዳይመልሱት ፣ አቃጥ ላችሁ ፣ ወደ ፣ ባሕር ፣ በትኑት ፣ ብሎ ፣ አዟቸው ፣ ነበርና ፣ እንዲሁ ፣ አደረጉለት ፤ ደግሞም ፣ ሊኩርጉስ ፣ ምንም ፣ ሊመለስ ፣ በይችል ፣ የሰጣቸውን ፣ ሕግ ፣ እንዲጠ ብቁ ፣ አምኗቸው ፣ ነበርና ፣ እስፓርቶች ፣ ፭፻ ፣ ዓመት ፣ ሕጉን ፣ ጠብቀው ፣ ኖሩ ።

፰ ፤ መቸውንም ፣ እስፓርታ ፣ ሲባሉ ፣ ጀግኖችና ፣ አገራቸውን ፣ የሚወዱ ፣ ኃይ ለኞች ፣ ሕዝቦች ፣ ናቸው ። በልማዳቸው ፣ ከሠለጠኑ ፣ ሕዝቦች ፣ ይልቅ ፣ ያረ መጌ ፣ ሕዝብ ፣ ልማድ ፣ አለባቸው ።

፱ ፤ በአቴን ፣ ድራኮ ፣ ሶሎን ፣ የተባሉ ፣ ሁለት ፣ የታወቁ ፣ ሕግ ፣ ሰጪዎች ፣ ነበሩ ።

የድራኮ ፣ ሕግ ፣ እጅግ ፣ ብርቱ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ በደም ፣ እንጂ ፣ በቀለም ፣ አይጻፍም ፣ ይባላል ። ስለ ፣ አንዲት ፣ ትንሽ ፣ መተላለፍ ፣ ቅጣቱ ፣ የሞት ፣ ፍርድ ፣ ነው ። የር ሱም ፣ ሕግ ፣ አልቂየም ፤ ቶሎ ፣ ብሎ ፣ ተሻረ ።

፲፩ ፣ የሶሎን ፣ ሕግ ፣ የሆነ ፣ እንደሆን ፣ ቀለል ፣ ያለና ፣ በጥበብና ፣ በመልካም ፣ አኳኋን ፣ የታገገ ፣ ነው ። ለሕዝብም ፣ ጥቅም ፣ ያለው ፣ ነው ። ነገር ፣ ግን ፣ የአ ቴን ፣ ሕዝብ ፣ ቅሌተኞችና ፣ ልከስከሶች ፣ ስለሆኑ ፣ ሁልጊዜ ፣ የተሰጣቸውን ፣ ሕግ ፣ መለዋወጥ ፣ ይወዳሉ ።

፲፪ ፣ በዚህ ፣ ጊዜ ፣ አቴን ፣ ሬፑብሊክ ፣ ሆኖ ፣ ነበር ። እንደምታውቁት ፣ የሕ ዝብ ፣ መንግሥት ፣ ማለት ፣ ነው ። ወዲያው ፣ ሶሎን ፣ ሕጉን ፣ ካወጣ ፣ በኋላ ፣ ፒስ ስትራቱስ ፣ የተባለ ፣ ዓቢይ ፣ ገነን ፤ ካገር ፣ ውስጥ ፣ ተነሣና ፣ ከነልጆቹ ፣ ጭምር ፣ አምሳ ፣ ዓመት ፣ ገዛ ።

ጥያቄ ።

፩ ፣ አስፓርታ ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ? ከአቴን ፣ ወይም ፣ ከቴቤስ ፣ ወዴት ፣ ነው ?
አስፓርታ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? ሕጋቸው ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?
ሊኩርጉስ ፣ የነበረው ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ?
አካሄዱና ፣ ጠባዩ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ኑሮዋል ፣

፪ ፣ አስፓሮቶች ፣ ማዕዳቸውን ፣ ባደባባይ ፣ አድርርገው ፣ እንዲበሉ ፣ ሊኩርጉስ ፣ ያስተማራቸው ፣ ስለ ፣ ምንድነው ፣ ?
ለልጆቻቸውስ ፣ ምን ፣ አደረጉ ፣ ?
ለልጆች ፣ ስርቆትን ፣ ስለምን ፣ ፈቀደ ፣ ?

፫ ፣ ስለ ፣ ገንዘብ ፣ ምን ፣ ሕግ ፣ ተደረገ ፣ ?
የአስፓርቶች ፣ ብር ፣ ምንድነው ፣ ?

፬ ፣ የልጆቻቸው ፣ አስተዳደግ ፣ እንዴት ፣ ነበር ፣ ?
ስካርን ፣ እንዲጸየፉ ፣ ያስተማራቸው ፣ እንዴት ፣ ናፖል ፣ ?

፭ ፣ ሊኩርጉስ ፣ ገና ፣ አገር ፣ ለቆ ፣ ሳይሄድ ፣ አስፓርቶችን ፣ ምን ፣ ብሎ ፣ አል ማላቸው ፣ ?

፮ ፣ የአስፓርቶች ፣ ሕግ ፣ ሰጪ ፣ ፍጻሜው ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ?

፯ ፣ አስፓርቶች ፣ እርሱ ፣ ያወጣላቸውን ፣ ሕግ ፣ ለስንት ፣ ዘመን ፣ ጠበቁት ፣ ?

፰ ፣ ድራኮና ፣ ሶሎን ፣ እንደ ፣ ምን ፣ ሆኑ ፣ ?

፱ ፣ የሶሎን ፣ ሕግ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

፲ ፣ አቴኖች ፣ እንደ ፣ ምን ፣ ያሉ ፣ ናቸው ፣ ?
የአቴን ፣ አገዛዝ ፣ እንዴት ፣ ነበር ፣ ?
ዓቢይ ፣ ገነን ፣ ሆኖ ፣ መንግሥቱን ፣ የያዘው ፣ ማነው ፣ ?
የአቴን ፣ መንግሥት ፣ አምሳ ፣ ዓመት ፣ ሙሉ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ?

ምዕራፍ ፡ ፫፭ ፡ ኤውሮጳ ።

ከፋርስ ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ እንዲት ፡ እንደ ፡ ተደረገ ።

፩ ፤ አምስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከዘመን ፡ ክርስትና ፡ በፊት ፡ ዳርዮስ ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ተግሪክ ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ አደረገና ፡ የርሱ ፡ ጄኔራል ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ መርከቦችና ፡ የሚሊዮን ፡ እኩሌታ ፡ የሚሆን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ይዞ ፡ አገሪቱን ፡ ወረራት ። ከአቴን ፡ ወገን ፡ ከወሥር ፡ ሺሕ ፡ የበለጡ ፡ ወታደሮች ፡ አልነበሩም ።

፪ ፤ ዳርዮስ ፡ ስሚቱ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ግሪክን ፡ አሸንፋለሁ ፡ ነበር ። ድል ፡ ሰለ ማድረጉ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጌጥ ፡ ሐውልት ፡ ለማሠራት ፡ ብሎ ፡ የተጠረበ ፡ ብዙ እብነ ፡ በረድ ፡ አስጭኖ ፡ ነበር ። የአቴን ፡ ሰዎች ፡ በሰንሰለት ፡ እየሆኑ ፡ ወደፋ ርስ ፡ እንዲላኩ ፡ ጄኔራሉን ፡ አዘት ፡ ነበር ።

፫ ፤ የአቴናች ፡ ጄኔራል ፡ ሚልቲያድስ ፡ ይባላል ። ትንሽ ፡ ወታደሮቹን ፡ ይዞ ፡ ስፍር ፡ ቊጥር ፡ የሌለውን ፡ የፋርስን ፡ ጦር ፡ ማራቶን ፡ በሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ገጠመው ። ይህም ፡ ከሰሜን ፡ ምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ከአቴን ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ የራቀ ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ የተሠራ ፡ አንድ ፡ ከተማ ፡ ነው ።

፬ ፤ ጀግኖቻቸው ፡ ሲዋጉ ፤ ሽማግሎችና ፡ ባላገሮቹ ፤ ሴቶችና ፡ ሕፃናቱ ፡ በከተ ማው ፡ በአቴን ፡ ሆነው ፡ የጦር ፡ ወሬ ፡ ለመስማት ፡ በታላቅ ፡ ናፍቆት ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበር ። ሚልትያድስ ፡ ድል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፋርሶች ፡ ድል ፡ የሆነውን ፡ ጭፍራ ፡ እያባረሩ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ነድተው ፡ ከተማውንም ፡ በእሳት ፡ እንዲያቃጥሉት ፡ ያውቁ ፡ ነበር ።

፭ ፤ በድንገት ፡ ክፉኛ ፡ ቊስሎ ፡ የነበረ ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ ደም ፡ ለብሶ ፡ በከተ ማው ፡ ገበያ ፡ ውስጥ ፡ ሲሮጥ ፡ ታየ ። ከጦር ፡ ውስጥ ፡ ሲሮጥ ፡ መምጣቱ ፡ የጦር ፡ ወሬ ፡ ለመንገር ፡ ነው ። ደሙ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ያገሳ ፡ ነበርና ፡ ፋርሶች ፡ ድል ፡ አድር ገው ፡ ሸሽቶ ፡ የመጣ ፡ መስሎዋቸው ፡ ሕዝቡ ፡ በጣም ፡ ደነገጡ ።

፮ ፤ ዙሪያውን ፡ ከበው ፡ ሚልትያድስና ፡ ጦሩ ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ እያሉ ፡ በጥያቄ ፡ ያስቸኩሉት ፡ ጀመር ። ወታደሩ ፡ ደክሞት ፡ ያመጣውን ፡ ወሬ ፡ ለመናገር ፡ ስላ ቃተው ፡ ጦሩን ፡ መርጐዝ ፡ ብሎ ፡ ተደግፎ ፡ ቁሞ ፡ ነበር ።

፯ ፤ ግን ፡ ባለ ፡ ኃይሉ ፡ እየጮኸ ፡ ያገሬ ፡ ሰዎች ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ ድሉ ፡ የኛ ፡ ሆኖዋል ፡ አለና ፡ በጣም ፡ ከመጮሁ ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ዘፍ ፡ ብሎ ፡ ወድቆ ፡ ሞተ ።

፰ ፤ የአቴን ፡ ሰዎች ፡ ጀግናውን ፡ አርበኛ ፡ ሚልትያድስን ፡ ምንም ፡ አላመሰገኑ ትም ። እርሱ ፡ አገሩን ፡ በባርነት ፡ ከመገዛት ፡ ያዳነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ዋጋ ፡ አድርጎ ፡ ከነሱ ፡ የሚፈልግባቸውን ፡ የወይራውን ፡ ቅጠል ፡ ጐንጕነው ፡ እንደዘውድ ፡ አድርገው ፡ ሠርተው ፡ ሊሰጡት ፡ ነበር ። ይህም ፡ በግሪክ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ለጀግና ፡ የሚሰጥ ፡ የከበረ ፡ የማዕርግ ፡ ምልክት ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይኸ

ንኑ ፣ እምቢ ፣ ብለው ፣ ከለከሉት ፣ እንጂ ፣ አልሰጡትም ። በኋላም ፣ በአንድ ፣ ትንሽ ፣ ነገር ፣ ተከሰሰና ፣ ካሣ ፣ ፱ ፣ ፓውንድ ፣ እንዲከፍል ፣ ተፈረደበት ። ሚልትያድስም ፣ ይህን ፣ ለመክፈል ፣ ብዙ ፣ ገንዘብ ፣ ያለው ፣ ሰው ፣ አልነበረምና ፣ በእስር ፣ ቤት ፣ ሞተ ።

፱ ፤ ከማራቶን ፣ ጦርነት ፣ በኋላ ፣ ግሪኮች ፣ ፋርሶችን ፣ ተግሪክ ፣ አገር ፣ እያክለበለቡ ፣ አስወጡዋቸው ። ዳርዮስም ፣ እንደ ፣ገና ፣ ግሪኮችን ፣ እወጋለሁ ፣ ብሎ ፣ ሲሰናዳ ፣ ስለ ፣ ሞተ ፣ ዘርክስ ፣ የተባለ ፣ ልጁ ፣ እንደ ፣ገና ፣ ጠቡን ፣ አደሰው ። ዘርክስ ፣ እንደ ፣ገና ፣ ግሪክን ፣ እወጋለሁ ፣ ብሎ ፣ ሁለት ፣ ሚሊዮን ፣ ወታደር ፣ ይዞ ፣ ግሪክን ፣ እንደ ፣ ወረራትና ፣ በዚያም ፣ ያገኘውን ፣ መከራ ፣ ሁሉ ፣ በፊት ፣ በጻፍሁት ፣ በፋርስ ፣ ታሪክ ፣ ነግሪያችኋለሁ ።

ጥ ያ ቄ ።

ፋርስ ፣ ከግሪክ ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ?

፩ ፤ ዳርዮስ ፣ ከግሪክ ፣ ጋር ፣ የተዋጋው ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ? የፋርስ ፣ ኃይል ፣ እንዴት ፣ ነበር ፣ ? የአቴኖችስ ፣ ጕልበት ፣ እንዴት ፣ ነበር ፣ ?

፪ ፤ ምን ፣ እብነ ፣ በረድ ፣ ነው ፣ ? ዳርዮስ ፣ ምን ፣ (አዘዘ) ትእዛዝ ፣ ሰጠ ?

፫ ፤ የአቴኖች ፣ ጀኔራል ፣ ማን ፣ ነበር ፣ ? ግራቶን ፣ ወዴት ፣ ነበር ፣ ?

፬ ፤ በአቴን ፣ የቄዩት ፣ እንደምን ፣ ሆኑ ፣ ?

፭ ፤ ከማራቶን ፣ ምን ፣ መልክተኛ ፣ (ሄደ) ተላከ ፣ ? ግራቶን ፣ ከአቴን ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ?

፮ ፤ ከእስፓርታ ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ? መልክተኛው ፣ ምን ፣ መልክት ፣ ይዞ ፣ መጣ ፣ ?

፯ ፤ ሚልትያድስን ፣ አቴኖች ፣ እንዴት ፣ አድርገው ፣ ተቀበሉት ፣ ? የርሱ ፣ ፍጻሜ ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ?

፰ ፤ ግራቶን ፣ ላይ ፣ ከተዋጉ ፣ በኋላ ፣ ፋርሶች ፣ እንዴት ፣ ሆኑ ፣ ? ዳርዮስ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? ዘርክስ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? በፋርስ ፣ ታሪክ ፣ ምን ፣ ታነባለህ ፣ ?

ምዕራፍ ፣ ፭፮ ፤ ኤውሮጳ ።

ስለ ፣ አቴን ፣ ጕዳይ ።

፩ ፤ ከፋርስ ፣ ጦርነት ፣ በኋላ ፣ በአቴን ፤ ሲሞን ፤ አርስቲድ ፣ ፔሪክልስ ፣ የተባሉ ፣ የታወቁ ፣ ሰዎች ፣ ነበሩ ። ፔሪክልስ ፣ ወዲያው ፣ በሬፑብሊክ ፣ ውስጥ ፣ ዋና ፣ ሆነ ። ፔሪክልስ ፣ የመንግሥት ፣ ዋና ፣ ሆኖ ፣ ሳይሾም ፣ አስቀድሞ ፣ አቴን ፣ የበለጠ ፣ ገናናነት ፣ አልነበራትም ።

፪ ፤ ታላላቅ ፣ ያማሩ ፣ ቤቶች በመሥራት ፣ ከተማዪቱን ፣ አስጌጣት ። በቅኔና ፣ በግጥም ፣ ስመ ፣ ጥሩ ፣ ሆነች ። የእጅ ፣ ሥራም ፣ አስተማራት ። መቅደሶችንና ፣ ሐውልትን ፣ ሥዕልንም ፣ እንደዚህ ፣ ያለውን ፣ ያስጌጠ ፣ እሱ ፣ ነው ። ነገር ፣ ግን ፣ አቴኖች ፣ ምስጋና ፣ የሌላቸው ፣ ወረተኞችና ፣ መንግሥታቸውን ፣ ጠቃሚ ፣

የሆነውን ፣ ዋናውን ፣ ሰው ፣ የሚንቁ ፣ ስለ ፣ ሆኑ ፣ ፔሪክልስን ፣ አላከበሩትም ።

፫ ፤ በኋለኛው ፣ ጊዜ ፣ እሱው ፣ መሪ ፣ ሆኖ ፣ ሳለ ፣ በአቴን ፣ ታላቅ ፣ መቅሠፍት ፣ ተነሣና ፣ ከሕዝቡ ፣ አያሎች ፣ በብሽታ ፣ ወደቁ ። እኩሉም ፣ ሞቱ ። እየሞተ ፣ የተ ጋደመው ፣ በመንገዱ ፣ ሁሉ ፣ ሬሳ ፣ በሬሳ ፣ ላይ ፣ ሆኖ ፣ ይታይ ፣ ነበር ።

፬ ፤ ለዚህ ፣ በሽታ ፣ መሥዋዕት ፣ የሆነው ፣ አንዱ ፣ ደምቆ ፣ ይታይ ፣ የነበር ፣ ፔሪክ ልስ ፣ ነው ። ወደሞት ፣ አፋፍ ፣ ሲቃረብ ፣ አንዱ ፣ ወዳጁ ፣ የሆነ ፣ ስለ ፣ አደረገው ፣ ሥራ ፣ ሁሉ ፣ እጅግ ፣ ቢያመሰግነው ፣ ታላቁ ፣ ክብሬ ፣ ይህ ፣ ነው ። በሠራሁት ፣ ሥራ ሁሉ ፣ ከአቴን ፣ ሕዝብ ፣ ያሳዘንሁት ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ አይገኝም ፣ ሲል ፣ ፔሪክልስ ፣ መለሰለት ።

፭ ፤ ፔሪክልስ ፣ ሳይሞት ፣ ገና ፣ ከሦስት ፣ ዓመት ፣ በፊት ፣ በአቴኖችና ፣ በእስፓር ታዎች ፣ መኻከል ፣ ጦርነት ፣ ተጀምሮ ፣ ነበር ። የግሪክ ፣ ዋናች ፣ መንግሥታት እነዚህ ፣ ሁለቱ ፣ ስለ ፣ ነበሩ ፣ እኔ ፣ እበልጥ ፣ እኔ ፣ እበልጥ ፣ በመባባል ፣ ይቃኑ ፣ ነበር ። በዚያ ፣ አውራጃ ፣ ባሉ ፣ በግሪክ ፣ መንግሥታት ፣ ሁሉ ፣ ፔሎፖኔሱስ ፣ የሚሉት ፣ ብርቱ ፣ ጦርነት ፣ ተነሣ ። ይህም ፣ ጠብ ፣ እስከ ፳፯ ፣ ዓመት ፣ ቂየ ።

፮ ፤ በዚሁ ፣ ጦርነት ፣ ውስጥ ፣ ሳሉ ፣ አንድ ፣ ለዐይን ፣ ደመቅ ፣ ብሎ ፣ የሚታይ ፣ አልስቢ ያድስ ፣ የተባለ ፣ ከአቴኖች ፣ መኻከል ፣ ተነሣ ። ይህም ፣ ለአቴኖች ፣ የተስማማና ፣ በመልኩም ፣ የተዋበ ፣ መልከ ፡ ቀና ፣ ሰው ፣ ነበር ። ከቶውንም ፣ አንድ ፣ ዘመን ፣ ሕዝቡ ፣ እጅግ ፣ አድርገው ፣ አፈቀሩትና ፣ ሥልጣኑ ፣ ሁሉ ፣ በእጁ ፣ ሆነ ። ዳሩ ፣ ግን ፣ የራሱን ፣ ክብር ፣ ፈላጊ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ ምንም ፣ ገንዘብ ፣ አልነበረውም ፤ ገንዘብ ፣ ያጥረው ፣ ነበር ።

፯ ፤ የብዙ ፣ ሁከት ፣ ምክንያት ፣ ሆነ ፣ ሁከቱም ፣ በግሪክ ፣ አገር ፣ ሁሉ ፣ እንጂ ፣ በርሱ ፣ አገር ፣ ከተማ ፣ ብቻ ፣ አልነበረም ። በመጨረሻው ፣ ሰው ፣ ሁሉ ፣ እንደ ጠላው ፣ ዐወቀና ፤ በትኒሽ ፣ እስያ ፣ ፍራይጂያ ፣ ወደተባለች ፣ መንደር ፣ ሄደና ፣ ቲማንድራ ፣ ከምትባል ፣ ሴት ፣ ዘንድ ፣ ተቀመጠ ።

፰ ፤ ጠላቶቹ ፣ ሊያስገድሉት ፣ ሰዎች ፣ ሰደዱበት ። እነዚህም ፣ ሄዱና ፣ የተቀመ ጠበትን ፣ ቤት ፣ አሳት ፣ ለቀቁበት ። አልሲቢያድስ ፣ ግን ፣ ጀግና ፣ ሰው ፣ ነበርና ፣ ሰይፉን ፣ እንደ ፣ መዘዘ ፣ ከጠላቶቹ ፣ ጋር ፣ ለመዋጋት ፣ ወጣ ። እነርሱ ፣ ግን ፣ ርቀው ፣ ቆመው ፣ ነበሩና ፣ ወርውረው ፣ በጦር ፣ ወጉትና ፣ ሬሳውን ፣ ቲማ ንድራ ፣ ትቅበረው ፣ ብለው ፣ ትተውላት ፣ ሄዱ ።

፱ ፤ የፔሎፖኔሲያን ፣ ጦርነት ፣ በአቴኖች ፣ ላይ ፣ ታላቅ ፣ መከራ ፣ አመጣባቸው ። እስፓርቶች ፣ ድል ፣ አድርገው ፣ የከተማቸውን ፣ ግንብ ፣ አፍርሰው ፣ ደለደሉት ። የማጥፋታቸው ፣ ሥራ ፣ እየበዛ ፣ በሄደ ፣ ጊዜ ፣ ድል ፣ የማድረጋቸው ፣ ደስታ ፣ በግጥምና ፣ በዘፈን ፤ በሙዚቃ ፣ እየሆነ ፣ ተዘፈነበት ።

፲ ፤ ከዚህ ፣ ወዲያ ፣ የአቴናን ፣ ሕዝብ ፣ የእስፓርቶች ፣ ፴ ፣ ሹማምት ፣ ገዙዋቸው ። እነዚህም ፣ የአቴን ፣ ግፈኞች ፣ ገዦች ፣ ተባሉ ። ሥልጣናቸውም ፣ ለሦስት ፣ ዓመት ፣

ብቻ ፣ ሆኖ ፣ ቀረ ። ትራሲቡሉስ ፣ የተባለ ፣ አገሩን ፣ ወዳጅ ፣ የሆነ ፣ አንድ ፣ የአቴን ፣ ሰው ፣ ነጻነታቸውን ፣ ለመመለስ ፣ ያገሩን ፣ ሰዎች ፣ አበረታቸው ።

፲፩ ፤ ሠላሳው ፣ ግፈኞች ፣ ገዦች ፣ ሸሽተው ፣ ለቀው ፣ ሄዱ ። ትራሲቡልስ ፣ ግን ፣ የክብርና ፣ የማዕርግ ፣ ሽልማት ፣ የሚሆን ፣ ከሁለት ፣ የወይራ ፣ ልምጭ ፣ የተሠራ ፣ ዘውድ ፣ የመሰለ ፣ ተሸለመ ። ፊት ፣ እንደ ፣ ተናገርሁት ፣ ይህ ፣ ታላቅ ፣ የክብር ፣ ምልክት ፣ ነው ። እንደ ፣ ገና ፣ የአቴን ፣ መንግሥት ፣ ተመለሰና ፣ እንደ ፣ ቀድሞው ፣ ሆነ ። ይህም ፣ የሆነው ፣ ፬፻፫ ፣ ዓመት ፣ ከክርስቶስ ፣ በፊት ፣ ነው ።

ጥያቄ ።

፩ ፤ በአቴን ፣ ሦስት ፣ ዋና ፣ ዋና ፣ ሰዎች ፣ የነበሩ ፣ አነግናቸው ፣ ? አቴናች ፣ ፔሪክልን ፣ እንዴት ፣ አደረጉት ፣ ?

፪ ፤ ለአቴኖች ፣ ምን ፣ ሠሩላቸው ፣ ? የአቴናች ፣ ጠባይ ፣ እንዴት ፣ ኑሮዋል ፣ ?

፫ ፤ በገር ፣ ላይ ፣ የመጣው ፣ መቅሠፍት ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ?

፬ ፤ ፔሪክል ፣ ታሞ ፣ በዓዕር ፣ ሳለ ፣ ምን ፣ አለ ፣ ?

፭ ፤ ፔሪክል ፣ ሳይሞት ፣ ሦስቱን ፣ ዓመት ፣ ምን ፣ ተጀምሮ ፣ ነበር ፣ ?

አቴኖችና ፣ እስፓርቶች ፣ እንዴት ፣ ሆኑ ፣ ? የፔሎፖኔሲያን ፣ ጦርት ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ቈየ ፣ ?

ተግሪክ ፣ አገር ፣ ፔሎፖኔሲያ ፣ የተባለው ፣ ክፍል ፣ የቱ ፣ ነው ፣ ?

ለፔሎፖኒስ ፣ የተጨመሩለት ፣ አውራጆች ፣ የትኞች ፣ ናቸው ፣ ? መልስ ፣ አራዲያ ፣ ላኮኒያ ፣ ሚሴኒያ ፤ ኤሊስ ፤ አርጎሊስ ፤ አካይይ ፤ ሲሲዮን ፤ ቆሮንቶስ ፣ ናቸው ።

፮ ፤ አልሲቢያድስ ፣ እንደምን ፣ ሆነ ፣ ?

፯ ፤ ምን ፣ አገኘው ፣ ?

፰ ፤ በምን ፣ ምክንያት ፣ ሞተ ፣ ?

፱ ፤ የፔሎፖኔሲያን ፣ ጦርነት ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? እስፓርቶች ፣ እንደምን ፣ ሆኑ ፣ ?

፲ ፤ ሠላሳው ፣ ግፈኞች ፣ ካፒቴኖችና ፣ ትራስቡሉስ ፣ እንዴት ፣ ሆኑ ፣ ?

፲፩ ፣ እነዚህን ፣ ግፈኞች ፣ እንደምን ፣ አስወገዳቸው ፣ ? ከክርስቶስ ፣ በፊት ፣ ፬፻፫ ፣ ዓመት ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ?

ምዕራፍ ፣ ፭፯ ፣ ኤውሮጳ ።

ስለ ፣ ቴባን ፣ ጦርነት ፣ አጀማመር ።

፩ ፤ ቴቤስ ፣ የታወቀ ፣ የግሪክ ፣ ከተማ ፣ ሆነ ። ይህም ፣ የቢዮቲያ ፣ መንግሥት ፣ ዋና ፣ ነበር ። በቴበችና ፣ በእስፓርቶች ፣ መኻከል ፣ ጦርነት ፣ የተጀመረበት ፣ አኳኋን ፣ እንደሚከተለው ፣ ነው ። ፈቤዳስ ፣ የተባለ ፣ የእስፓርታ ፣ ጀኔራል ፣ የቴበች ፣ ምሽግ ፣ የነበረችውን ፣ ካድሚያን ፣ በግፍ ፣ ያለ ፣ አገባብ ፣ ይዞ ፣ ስለ ፣ ነበረ ፣ ቴበች ፣ ልቀቅ ፣

አሉት ፣ እስፓርቶች ፣ ግን ፣ እንኳን ፣ ሊለቁ ፣ የራሳቸው ፣ ገንዘብ ፣ አድርገውት ፣ ምሽጋቸውን ፣ አጠንክረው ፣ መሸጉ ።

፪ ፤ ከቴቦች ፣ ወገን ፣ አገሩን ፣ ወዳጅ ፣ ፔሎፒዳስ ፣ የተባለ ፣ አንድ ፣ ጐልማሳ ፣ ምሽጉን ፣ ለማስመለስ ፣ አንድ ፣ የብልሀት ፣ ሥራ ፣ ሠርቶዋል ። ዐሥራ ፣ ሁለት ፣ ጓደኞቹን ፣ ያዘና ፣ በየደረታቸው ፣ የብረት ፣ ሣህን ፣ ለጥፈው ፣ ሁሉም ፣ ሰይፍ ፣ ሰይፋቸውን ፣ በየወገባቸው ፣ ከታጠቁ ፣ በኋላ ፣ በላይ ፣ የሴት ፣ ቀሚስ ፣ አጠለቁበት ። እንደዚህ ፣ ሴቶች ፣ መስለው ፣ ወደ ፣ ካድሚያ ፣ ሄደው ፣ ከበር ፣ ሲደርሱ ፣ ክፈቱልን ፣ ቢሉ ፣ ለመግባት ፣ ተፈቀደላቸው ።

፫ ፤ የእስፓርታ ፣ አለቆችና ፣ መኳንንት ፣ ተሰብስበው ፣ ታላቅ ፣ ግብር ፣ አድርገው ፣ ነበር ። በገበታው ፣ ራስ ፣ የነበረ ፣ አርቺያስ ፣ የተባለ ፣ የእስፓርታ ፣ አዛዥ ፣ ነው ። እርሱና ፣ አብረውት ፣ ገበታውን ፣ ከበው ፣ የነበሩት ፣ ሁሉ ፣ በግብሩ ፣ በጣም ፣ ደስ ፣ ይላቸው ፣ ነበር ። የሴት ፣ ልብስ ፣ ለብሰው ፣ በቅጥሩ ፣ ግቢ ፣ ዐሥራ ፣ ሁለት ፣ ሰዎች ፣ መግባታቸውን ፣ ከቶ ፣ ማንም ፣ አላሰበም ።

፬ ፤ የግብሩ ፣ ማግር ፤ የበዓሉ ፣ መድመቅ ፤ ደስታውና ፣ ውበቱ ፤ እጅግ ፣ ከፍ ፣ ብሎ ሳለ ፣ ዐሥራ ፣ ሁለቱ ፣ ጀግኖች ፣ ለብሰውት ፣ የነበረውን ፣ የሴት ፣ ልብስ ፣ አውልቀው ፣ በታዩ ፣ ጊዜ ፣ ያዳራሹ ፣ ፋና ፣ ፀዳል ፣ በደረታቸው ፣ ካለው ፣ ልብስና ፣ ከተመዘዘው ፣ ሰይፍ ፣ ላይ ፣ ሲያርፍ ፣ ለዐይን ፣ አንጸባረቀ ።

፭ ፤ ፔሎፒዳስ ፣ ጀግኖች ፣ ከሆኑት ፣ ካሥራ ፣ ሁለቱ ፣ ጓደኞቹ ፣ ጋር ፣ የእስፓርቶችን ፣ ግብር ፣ በሰይፍ ፣ ሲጠርገው ፣ እስፓርቶች ፣ ስለ ፣ ደነገጡ ፣ ለመከላከል ፣ አልቻሉም ። አርቺያስና ፣ ከርሱ ፣ ጋር ፣ የነበሩትም ፣ ሁሉ ፣ ከገበታው ፣ ሳይነሡ ፣ እዚያው ፣ ላይ ፣ እንደ ፣ ተመቱ ፣ ቀሩ ።

፮ ፤ እንደዚህ ፣ አድርገው ፣ ቴቢያኖች ፣ ምሽጋቸውን ፣ አስመለሱ ። ነገር ፣ ግን ፣ ወዲያው ፣ በቶሉ ፣ እስፓርቶች ፣ በቴቢያኖች ፣ ላይ ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ጦርነት ፣ ባነሡ ፣ ጊዜ ፣ አያሎች ፣ የግሪክ ፣ መንግሥታት ፣ ርዳታቸውን ፣ ወደ ፣ እስፓርቶች ፣ ሰደዱ ። በመጨረሻው ፣ ቴቦች ፣ ድል ፣ ሆነው ፣ ጭራሽ ፣ እንደ ፣ ጠፉ ፣ ይመስላል ።

፯ ፤ ነገር ፣ ግን ፣ ኢፓሚናንዳስ ፣ የተባለ ፣ አንድ ፣ ብልሀተኛ ፣ ጀግና ፣ ጄኔራል ፣ ነበራቸው ። ስድስት ፣ ሺሕ ፣ ቴቢያኖችን ፣ ይዞ ፣ በንጉሣቸው ፣ በክሊምብሮቱስ ፣ እየተመሩ ፣ የመጡትን ፣ ሯጩቱን ፣ ሺሕ ፣ እስፓርታኖች ፣ ሊውክትራ ፣ ላይ ፣ ተዋጋቸውና ፣ ፈጽሞ ፣ ድል ፣ አደረጋቸው ፣ ክሊምብሮቱስም ፣ ከ፲፬፻—ወታደሮቹ ፣ ጋር ፣ እዚያው ፣ ላይ ፣ ታረደ ።

ጥ ያ ቄ ።

ቴቤስ ፣ ከእስፓርታና ፣ ከማራቶን ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ?

፩ ፤ ቴቤስ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? ቢምቲያ ፣ ከግሪክ ፣ በየትኛው ፣ ክፍል ፣ ነው ፣ ? በቴቤስና ፣ በእስፓርታ ፣ መኻከል ፣ ቀድሞውን ፣ ጦርነት ፣ እንዴት ፣ ተጀመረ ፣ ?

፪ ፤ ፔሎፒዳስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ስለ ፡ ፔሎፒዳስና ፡ ጓደኞቹ ፡ ተናገር ።

፫ ፤ ይህ ፡ የድፍረት ፡ አጀማመር ፡ ተፈጸመ ፡ ወይ ፡ ?

፮ ፤ በቴቤስ ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ ያደረገ ፡ ማነው ፡ ?

፯ ፤ ኤፓሚኖዳስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ጦሩ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? የእስፓርቶች ፡ ኃይል ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
የእስፓርቶች ፡ መሪ ፡ ማን ፡ ነበር ፡ ? ሉክትራ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡?ከቴቤስ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
ከእስፓርታስ ፡ ? ከአቴንስ ፡ ? ቴቢያኖች ፡ ድል ፡ አገኙን ፡ ?

ምዕራፍ ፡ ፫፯ ፡ ኤውሮጳ ።

የቴቢያን ፡ ጦርነት ፡ መከናወን ።

፩ ፤ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ከነበሩት ፡ ደጎች ፡ ከተባሉት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ኤፓሚኖዳስ ፡ የተባለው ፡ የቴቢያን ፡ ጀኔራል ፡ ነው ። አገር ፡ መውደድንና ፡ ጭከናን ፤ በጎ ፡ ምግባርንም ፡ አስተካክሎ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ሐሰት ፡ ነገር ፡ ተከንፈሩ ፡ ወጥቶ ፡ አያውቅም ፡ ይባላል ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋና ፡ የሚያሰጠው ፡ ነው ።

፪ ፤ በጀግንነት ፡ አገሩን ፡ ላዳነ ፡ እንደ ፡ ኤፓሚኖዳስ ፡ ላለ ፡ ሰው ፡ ቴቢያኖች ፡ ታላቅ ፡ ምስጋና ፡ መስጠት ፡ ይገባቸው ፡ ነበር ። እውነት ፡ ነው ፡ አያሎች ፡ ከሕዝቡ ፡ ደግነት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ አከበሩት ። ነገር ፡ ግን ፡ ለመናገር ፡ እጅግ ፡ አዝናለሁ ። ከቶ ፡ ለትልቅ ፡ ሰውና ፡ ለደግ ፡ ሰው ፡ ጠላት ፡ አይጠፋለትም ።

፫ ፤ ደግነቱም ፡ ታላቅነቱም ፡ ተግሣጽ ፡ ሆነበትና ፡ እንደ ፡ ወንጀል ፡ ተቈጠረበት ። እንደዚህ ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ በየጊዜው ፡ እንደሚደረግ ፡ በኤፓሚኖዳስም ፡ የተደረገበት ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

፬ ፤ ኤፓሚኖዳስ ፡ ከቴቢያኖች ፡ መኻከል ፡ ጠላቶች ፡ ነበሩት ። «ካሁን ፡ ቀደም ፡ በሕግ ፡ ከተወሰነው ፡ አብልጠህ ፡ የጦሩን ፡ ወታደር ፡ ስታዘው ፡ ቈይተሀል ፡ » ብለው ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ሊያስፈርዱበት ፡ ሞክረው ፡ ነበር ።

ይህን ፡ ያደረገበት ፡ ምክንያት ፤ አገሩን ፡ ከጥፋት ፡ ለማዳን ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ዳኛው ፡ በደለኛ ፡ አያሰኘውም ፡ ብሎ ፡ ፈረደለትና ፡ ለቀቀው ።

፭ ፤ ደግሞ ፡ እንደሚቻላቸው ፡ ያህል ፡ ለማዋረድ ፡ ሲሉ ፡ የቴቤስን ፡ ጐዳና ፡ በሚጠርጉ ፡ ላይ ፡ ቢሾሙት ፡ ቴቤያኖች ፡ ምስጋና ፡ የሌላቸው ፡ በመሆናቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ማዋረዳቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያውቃልና ፡ ኤፓሚኖዳስ ፡ በዚህ ፡ አላዘነም ፤ ወይም ፡ አልተቈጣም ። እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ከፍ ፡ የሚያደርገውና ፡ የሚያስከብረው ፡ የሚሠራበት ፡ ስፍራ ፡ ከሆነ ፤ እንዲሁም ፡ ሰው ፡ የሚሠራበትን ፡

ስፍራ ፣ ከፍ ፣ ሊያደርገውና ፣ ሊያስከብረው ፣ ይችላል ፣ ብሎ ፣ ይህን ፣ አዲስ ፣ የተቀበለውን ፣ ትእዛዝ ፣ ለመፈጸም ፣ ወጣ ። እንዲሁም ፣ የታወቀው ፣ ስመ ፣ ጥሩው ፣ ጀግና ፣ ጀኔራል ፣ በመንገድ ፣ ላይ ፣ የሚገኘውን ፣ ቊሻሻና ፣ ጕድፍ ፣ መጥረጊያ ውን ፣ ይዘ ፣ ሲጠርግ ፣ ታየ ።

፮ ፣ ጦርነቱ ፣ ገና ፣ አላላቀም ፣ ነበርና ፣ ቴቢያኖች ፣ ያለ ፣ ኤፓሚናዳስ ፣ ከቶ ፣ እንደ ማይሆንላቸው ፣ ስለ ፣ ተረዱት ፣ ከእጁ ፣ መጥረጊያውን ፣ ነጠቁና ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ሰይፍ ፣ አስጨብጠው ፣ ከቀድሞው ፣ የበለጠ ፣ ሥልጣን ፣ ሰጡትና ፣ ጠቅላይ ፣ የጦር ፣ አበጋዝ ፣ አደረጉት ።

፯ ፣ ጀኔራላቸው ፣ ኤፓሚናዳስ ፣ እስካለ ፣ ድረስ ፣ ቴቢያኖች ፣ እጅግ ፣ ኃይለኞች ፣ የግሪክ ፣ ሕዝብ ፣ ተባሉ ። የመጨረሻውን ፣ ድል ፣ ያደረገበት ፣ ስፍራ ፣ ማንቲኒያ ፣ ይባላል ። ነገር ፣ ግን ፣ ጦርነቱ ፣ በቴቢያኖች ፣ ላይ ፣ እጅግ ፣ በርትቶ ፣ ስለ ፣ ነበረ ፣ ኤፓሚናዳስ ፣ ጽኑ ፣ ውጊት ፣ ገጥሞ ፣ ሲዋጋ ፣ ከእስፓርቶች ፣ ወገን ፣ የሆነ ፣ አንድ ፣ ወታደር ፣ ደረቱን ፣ በጦር ፣ ወጋው ።

፰ ፣ በዚህ ፣ ጊዜ ፣ እስፓርቶች ፣ ያቈሰልነውን ፣ ሰው ፣ እንጨርሳለን ፣ ሲሉ ፣ ቴቢያኖች ፣ ግን ፣ የወደቀውን ፣ ጀኔራላቸውን ፣ አንሥተው ፣ ለመሄድ ፣ ሲሉ ፣ በቊስለው ፣ በኤፓሚናዳስ ፣ ዙሪያ ፣ እጅ ፣ ለእጅ ፣ ገጥመው ፣ በጨበጣ ፣ ተዋጉ ። በዚህ ፣ ክርክር ፣ ቴቢያኖች ፣ እስፓርቶችን ፣ አባረሩና ፣ ኤፓሚናዳስን ፣ ወታደሮቹ ፣ ተሸክመው ፣ ወደ ፣ ድንኳን ፣ ወሰዱት ።

፱ ፣ ወጌሻው ፣ ጦሩ ፣ ተቊስሉ ፣ ላይ ፣ የተነቀለ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ሰውዬው ፣ ያን ፣ ጊዜውን ፣ ይሞታል ፣ ብሎ ፣ ስለ ፣ አስጠነቀቀ ፣ ጦሩ ፣ እቊስሉ ፣ ላይ ፣ እንደ ፣ ተሰነቀረ ፣ ሳይነቀል ፣ ቄይቶ ፣ ነበር ። ኤፓሚናዳስ ፣ በጭንቅ ፣ ጣር ፣ ይዘት ፣ ሳለ ፣ ወገኖቹ ፣ ድል ፣ የማድረጋቸውን ፣ ወሬ ፣ ብቻ ፣ ይናፍቅና ፣ ያስብ ፣ ነበር ፣ እንጂ ፣ ለሕማሙ ፣ ትንሽም ፣ አላሰበ ።

፲ ፣ ቄይቶ ፣ ከውጊያው ፣ መልከተኛ ፣ መጥቶ ፣ እስፓርቶች ፣ ፈጽመው ፣ ድል ፣ ሆኑ ፣ ቴቢያኖች ፣ ድል ፣ አደረጉ ። ብሎ ፣ ቢነግረው ፣ ኤፓሚናዳስ ፣ መልካም ፣ ሆነ ፣ ብሎ ፣ ከተናገረ ፣ በኋላ ፣ ጦሩን ፣ ከቊስሉ ፣ እንደ ፣ ነቀለው ፣ ያን ፣ ጊዜውን ፣ ነፍሱ ፣ ወጣ ።

፲፩ ፣ ይህ ፣ የሆነው ፣ ከክርስቶስ ፣ በፊት ፣ ፫፻፷፫ ፣ ዓመት ፣ ነው ። ኤፓሚናዳስ ፣ ከሞተ ፣ በኋላ ፣ ቴቢያኖች ፣ ለቀሩት ፣ ግሪክች ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ የሚያስፈሩ ፣ አልሆኑም ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፣ ኤፓሚናዳስ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ሰው ፣ ኑሮዋል ፣ ?

፪ ፣ ቴቢያኖች ፣ ያመሰግኑት ፣ ኑሮዋልን ፣ ?

፫ ፣ እነዚህ ፣ ክፎች ፣ ደጉንና ፣ ታላቁን ፣ ሹማቸውን ፣ ኤፓሚናዳስን ፣ ያላመ ሰገኑት ፣ ስለምንድነው ፣ ?

፩ ፣ ቴቢያኖች ፣ ምን ፣ አስበው ፣ ኑረዋል ፣ ?
፭ ፣ ተዋረደን ? ፣ ምን ፣ አደረገን ፣ ?
፯ ፣ ቴቢያኖች ፣ ምን ፣ አገኙ ፣ ? ምን ፣ አደረጉ ፣ ?
፯ ፣ ኤፓሚናዳስ ፣ ጀኔራል ፣ ሳለ ፣ ቴቢያኖች ፣ እንዴት ፣ ነበሩ ፣ ?
የመጨረሻው ፣ ድል ፣ የትኛው ፣ ነው ፣ ? እንደምን ፣ ቁሰለ ፣ ? ማንቲኒያ ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ?
፰ ፣ ከቴቤስ ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ? ከእስፓርታ ፣ ከአቴን ፣ ከግራቶን ፣ ወዴት ፣ ነው ፧ ?
ከጦር ፣ ሜዳ ፣ ላይ ፣ ያነሣው ፣ ማነው ፣ ?
ሾተሉ ፣ እንደምን ፣ ሆነ ፣ ?
፱ ፣ የኤፓሚናዳስን ፣ አሙዋሙዋት ፣ በቀጥታ ፣ ተናገር ።
፲ ፣ ይህ ፣ የሆነው ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ? ከኤፓሚናዳስ ፣ ሞት ፣ በኋላ ፣ ቴቢያኖች ፣ እንዴት ፣ ሆኑ ፣ ?

ምዕራፍ ፣ ፭ኛ ፣ ኤውሮጳ ።

ስለ ፣ ጥንታውያን ፣ ግሪኮች ፣ ሃይማኖትና ፣ ተረት ።

፩ ፣ አሁን ፣ ግሪኮች ፣ ክብራቸው ፣ ከፍ ፣ ወደ ፣ አለበት ፣ ዘመን ፣ ደርሻለሁ ፣ ደግሞ መዋረዳቸውን ፣ ቶሎ ፣ ብዬ ፣ እነግራችኋለሁ ፣ ነገሩን ፣ ሳልጀምረው ፣ አስቀድሜ የግሪኮችን ፣ ሃይማኖትና ፣ ሌላም ፣ አያል ፣ ነገር ፣ ጥቂት ፣ ልበወራላችሁ ፣ የተገባ ይመስለኛል ።

፪ ፣ ግሪኮች ፣ ሦስት ፣ አማልክት ፣ እንዳሉ ፣ ያምናሉ ። እነዚህም ፣ ሴሊስቲያል ፣ ማሪን ፣ ኢንፈርናል ፣ ናቸው ። ለነሱ ፣ እንደሚመስላቸው ፣ የመጀመሪያው ፣ መኖሪያው ፣ በሰማይ ፣ ነው ። ሁለተኛው ፣ በባሕር ፣ ነው ። ሦስተኛው ፣ ከመሬት ፣ በታች ፣ ነው ፣ ይላሉ ። በደን ፣ ውስጥ ፣ ወይም ፣ በምንጭና ፣ በፈሳሽ ፣ ውሃ ፣ የሚኖሩ ፣ ከነዚህ ፣ በቀር ፣ ሌሎች ፣ ትንንሾች ፣ አማልክት ፣ አሉ ።

፫ ፣ መኖሪያቸውን ፣ በሰማይ ፣ ያደረጉት ፣ አማልክት ፣ ጁፒትር ፣ አፖሎ ፣ ማርስ ፣ መርኩር ፣ ባኩስ ፣ ቩልካን ፣ ጁኖ ፣ ሚኔርቫ ፣ ቤኑስ ፣ ዲያና ፣ ሴሬስ ፣ ቬስታ ፣ ናቸው ። ከነዚህ ፣ ሁሉ ፣ የሚበልጠው ፣ ጁፒትር ፣ ነው ። ነጐድጓድና ፣ መብረቅ ፣ በሆነ ፣ ጊዜ ፣ ግሪኮች ፣ ጁፒትር ፣ ተቈጥቶ ፣ ነጐድጓዱን ፣ በዙሪያው ፣ ሁሉ ፣ የወዘወዘው ፣ ይመስላቸው ፣ ነበር ።

፬ ፣ ግሪኮች ፣ ጁፒትርን ፣ ለማክበር ፣ ብለው ፣ የሠሩት ፣ አሊምፒክ ፣ የሚሉት ፣ ጨዋታ ፣ ነበራቸው ። ይህንንም ፣ ባራት ፣ ባራት ፣ ዓመት ፣ ክብር ፣ ያደርጉት ፣ ነበር ። ይህንንም ፣ ሲያደርጉ ፣ በእግር ፣ ሩጫ ፣ ወይም ፣ በፈረስ ፣ ማሽቀዳደም ፣ በሠረገላም ፣ መሽቀዳደም ፣ በዝላይም ፣ በትግልም ፣ በጡጫ ፣ በመማታት ፣ ነውና ፣ በአሊምፒክ ፣ ጨዋታ ፣ ይህን ፣ እንደ ፣ ታላቅ ፣ ከበሬታ ፣ ያስቡት ፣ ነበር ።

፭ ፤ አፖሎ ፣ የጁፒትር ፣ ልጅ ፣ ነው ። ፀሓይን ፣ የሚነዳት ፣ እሱ ፣ ነው ። አራት ፤ ፈረሶች ፣ ዕቃቸውን ፣ እንደ ተጫኑ ፣ አሉት ። እንደዛሬው ፣ ዘመን ፣ በማረ ፣ ሠረገላ ፣ ሁኖ ፣ ሌላ ፣ ሰው ፣ ሳያስቀምጥ ፣ ዘወትር ፣ ዓለምን ፣ ይዘራል ።

፮ ፤ የፀሓይን ፣ ሠረገላ ፣ ከመንዳት ፣ በቀር ፣ አፖሎ ፣ ራሱ ፣ የሙዚቃና ፣ የቅኔ ፤ የመድኃኒትና ፣ የረቂቅ ፣ ሥራ ፣ አምላክ ፣ ይባላል ። ወደፊት ፣ የሚሆነውን ፣ ለማ ወቅ ፣ ከዓለም ፣ ሁሉ ፣ የሚመጡ ፣ ሕዝብ ፣ በሚሰበሰቡበት ፣ በታወቀው ፣ ንግር ፣ በተነገረበት ፣ በዴልፊ ፣ ላይ ፣ ወርዶ ፣ ተቀምጧል ፣ ይላሉ ።

፯ ፤ ማርስ ፣ የጦር ፣ አምላክ ፣ ነው ፤ መርኩሪ ፤ የሌቦች ፣ አምላክ ፣ ነው ፤ ባኩስ ፤ የሰካሮች ፣ አምላክ ፣ ነው ፤ ቩልካን ፣ የቀጥቃጮች ፣ አምላክ ፣ ነው ፤ ቩልካን ፣ የታውቀ ፣ ብረት ፣ ሠራተኛ ፣ በመሆኑ ፣ ብረት ፣ በመዶሻ ፣ የሚመታ ፣ ነውና ፣ ከአሕዛብ ፣ አማልክት ፣ ሁሉ ፣ እርሱ ፣ እጅግ ፣ ጥቅም ፣ ያለው ፣ አምላክ ፣ ነው ።

፰ ፤ ቤኑስ ፤ የውበት ፣ አምላክ ፣ ትባላለች ። ምስሉዋም ፣ በቄንጆ ፣ ሴት ፣ መልክ ፣ የተበጀ ፣ ይመስላል ። ኩፒድ ፣ የተባለ ፣ ልጅ ፣ አላት ። እርሱም ፣ ያለጥፋት ፣ ሌላ ፣ አያውቅምና ፣ ቀስትና ፣ ፍላፃ ፣ ይዞ ፣ ሰዎችን ፣ ይነድፋል ። ሠረገላው ፣ እንደ ፣ አንድ ፣ ሹል ፣ ዛጐል ፣ ሁኖ ፣ ከወደ ፣ ኋላው ፣ ጅራቱ ፣ የዓሣ ፣ ጅራት ፣ ይመስላል ። በባሕር ፣ ሞገድ ፣ ላይ ፣ ሲሄድ ፣ በባሕር ፣ የሚኖሩ ፣ ትሪቶንስ ፣ የሚባሉ ፣ ፍጥረቶች ፣ በሠረገላው ፣ ዙሪያ ፣ ይከቡታል ።

፱ ፤ ፕሉቶ ፣ በትንንሾች ፣ አውራጃዎች ፣ የሚኖር አምላክ ፣ ነው ። በሚያስፈራ ፣ አስተያየት ፣ እየተመለከተ ፣ በድኝ ፣ ዙፋን ፣ ላይ ፣ መቀመጥ ፣ ይወዳል ። በአንድ ፣ እጁ ፣ በትረ ፣ መንግሥት ፤ በሁለተኛው ፣ እጁ ፣ ሁለት ፣ የቍልፍ ፣ መክፈቻዎች ፣ ይዟል ፣ ይላሉ ። ግሪኮች ፣ ከነዚህ ፣ አማልክት ፣ ሌላ ፣ ደግሞ ፣ እኩሌታ ፣ ሰውነታቸው ፣ ሰው ፣ ሆነው ፣ እኩሌታው ፣ አማልክት ፣ በሆኑት ፣ ጀግኖች ፣ ያምናሉ ። ከነዚህ ፣ ስመ ፣ ጥሩው ፣ ኃይሉና ፣ ጡንቻው ፣ የታወቀለት ፣ ሔርኩሌስ ፣ ነው ።

፲ ፤ ስለዚህ ፣ ነገር ፣ አንድ ፣ ትልቅ ፣ መጽሐፍ ፣ ካልጻፍሁ ፣ የጥንት ፣ ግሪኮች ፣ ስለ ሚያመልኩዋቸው ፣ ስለሚያሥቁ ፣ አማልክት ፤ ሁሉን ፣ ልነግራችሁ ፣ አልችልም ። ይህ ፣ በመደረጉ ፣ የግሪክ ፣ ባለቅኔዎች ፣ ስለ ስንፍና ፣ ቂጥረውታል ። ምንም ፣ የሚ ያሥቅ ፣ ተረት ፣ ቢሆን ፣ ከእንደዚህ ፣ ያለ ፣ ስንፍና ፣ በቀር ፣ የተሻለ ፣ ሃይማኖት ፣ ማውጣት ፣ ካልቻሉ ፣ እንዲህ ፣ ያለው ፣ መጽሐፍ ፣ ዋና ፣ ጥቅምነቱ ፣ እውነተ ኛው ፣ አምላክ ፣ ራሱን ፣ ለሰዎች ፣ መግለጡ ፣ አስፈላጊ ፣ መሆኑን ፣ ለማሳየት ፣ ነው ።

፲፩ ፤ አማልክቶቻቸው ፣ መቀለጃም ፣ ቢሆኑ ፣ ግሪኮች ፣ ያማረ ፣ ቤተ ፣ መቅደስ ፣ እየ ሠሩ ፣ ያከብሩዋቸዋል ። እንደዚህ ፣ ያለ ፣ እጅግ ፣ ያማረ ፣ ሕንጻ ፣ ከቶ ፣ መዋቲ ፣ የሆነ ፣ የሰው ፣ እጅ ፣ የሠራው ፣ አይመስልም ። በአገራችን ፣ ካሉት ፣ ቤተ ፣ ክር ስቲያናት ፣ እኩሌቶቹ ፣ የተሠሩት ፣ በጥንት ፣ በግሪኮች ፣ ቤተ ፣ ጣዖት ፣ አምሳል ፣ ነው ።

፲፪ ፤ የግሪክች ፣ ደንጊያ ፣ ጠራቢዎች ፣ የጣዖታቸውን ፣ መልክ ፣ የሚቀርጹት ፣ ከእብነ ፣ በረድ ፣ ደንጊያ ፣ ነው ። እነዚሁም ፣ ሥዕሎች ፣ ታላላቆችና ፣ ያማሩ ፣ የከበሩም ፣ ናቸው ። ሥራቸውን ፣ ለተመለከተው ፣ ጠራቢዎቹ ፣ ወደ ፣ ሰማይ ፣ ገብተው ፣ ተምረው ፣ የሠሩት ፣ ይመስላል ፣ እንጂ ፣ እንዲህ ፣ ያለ ፣ ሥራ ፣ በም ድር ፣ ወዴት ፣ አይተው ፣ ሠሩት ፣ ያሰኛል ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ግሪክ ፣ በጣም ፣ ከፍ ፣ ያለበት ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ?

፪ ፤ ግሪኮች ፣ በየትኞቹ ፣ አማልክት ፣ ያምናሉ ፣ ? ሦስት ፣ ክፍል ፣ የነበሩት ፣ አማልክት ፣ እነማን ፣ ናቸው ፣ ?
የያንዳንዱ ፣ መኖሪያ ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ? የሚያንሱት ፣ አማልክት ፣ የት ኞች ፣ ናቸው ፣ ?

፫ ፤ በሰማይ ፣ የሚኖሩት ፣ የትኞች ፣ ናቸው ፣ ? ጁፒትር ፣ ምንድን ፣ ነው ፣ ?

፬ ፤ አሊምፒስ ፣ የሚሉት ፣ የምን ፣ በዓል ፣ ነው ፣ ?

፭ ፤ አፖሎ ፣ ምንድ ፣ ነው ፣ ? ሠረገላውስ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

፮ ፤ ስለ ፣ አፖሎ ፣ ሴላ ፣ የምትናገረው ፣ አለህን ፣ ?

፯ ፤ ማርስ ፤ መርኩሪ ፤ ባኩስ ፤ ቩልካን ፤ ምንድናቸው ፣ ? ቬኑስ ፣ ምንድነው ፣ ? ኩፒድ ፤ ኔፕትን ፣ ምንድነው ፣ ? መኖሪያው ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ? እንዶ ምን ፣ ያለ ፣ ነው ፣ ?

፲ ፤ ፕሉቶ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ነው ፣ ? መኖሪያው ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ? ምን ፣ አደረገ ፣ ?

፲፩ ፤ ግሪኮች ፣ ሐሰተኞች ፣ አማልክቶቻቸውን ፣ እንዴት ፣ አድርገው ፣ ያከ ብራሉ ፣ ?
ቤተ ፣ ጣዖቱ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ነው ፣ ?

፲፫ ፤ ስለ ፣ ግሪኮች ፣ ሐውልቶች ፣ ምን ፣ ትላለህ ፣ ?

ምዕራፍ ፣ ፱ ፣ ኤውሮጳ ።

ስለ ፣ ግሪክ ፣ ፈላስፎች ።

፩ ፤ የግሪክ ፣ ፈላስፎች ፣ ከሰው ፣ ሁሉ ፣ ይልቅ ፣ እጅግ ፣ ብልሆቹ ፣ እኛ ፣ ነን ፣ የሚሉ ፣ ሰዎች ፣ ነበሩ ። ከነርሱም ፣ አያሌቹ ፣ በልዩ ፣ ልዩ ፣ ዘመን ፣ ነበሩ ። በዚህና ፣ በሚመጣው ፣ ምዕራፍ ፣ ስለታወቁት ፣ ፈላስፎች ፣ ጥቂት ፣ እናገራለሁ ።

፪ ፤ ጣሌስ ፣ የተባለው ፣ ፈላስፋ ፣ የተወለደው ፣ ከክርስቶስ ፣ በፊት ፣ በስድስትና ፣ በጷ ፣ መቶ ፣ ዓመት ፣ መኻከል ፣ ነው ። በርሱ ፣ ዘመን ፣ የግሪክ ፣ ሰባት ፣ ጠቢ ባን ፣ የተባሉ ፣ ሰባት ፣ ፈላስፎች ፣ ነበሩ ። ጣሌስ ፣ ከነዚህ ፣ ሁሉ ፣ የበለጠ ፣ ጠቢብ ፣ ተብሎ ፣ ይታሰባል ።